

የማፍት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

# ትንሣኤ



ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

ቁጥር ፩፻፵፫ | የሐምሌና የነሐሴ ወር ፲፱፻፹፪

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም/ አዘጋጅ መ ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

# ማውጫ ፡

## አርእስት

ገጽ

ደብዳቤዎች ............ ፩
ርእሰ አንቀጽ ዘኢዮትዮጵያ ተከሥተ ............ ፪
ቅዱስነታቸው በገነተ ጽጌ ቅ ጊዮርጊስ የተሠራውን ሙዚየም ቤት
መርቀው ከፈቱ ሙደንአስተመጡ ............ ፬
ዓይን ያለው በግብፅ ፖርት ሰኢድ ከተማ ............ ፮
በአዲስ አበባ ሀ ስብከት ፺ ካህናት ተመረቁ ............ ፲፩
የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ............ ፲፪
ቁርቁስና ኢየሉጣ ............ ፲፬
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፲፮
የሴቶች ዓምድ ............ ፲፯
ዜና ሊቃውንት ............ ፲፱
ጠባይህን አሻሽለሃል? ............ ፳
የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው ............ ፳፪
የደብረ ጽጌ ገዳም አጭር ታሪክ ............ ፳፬

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከሰላምታዬ ቀጥዬ አንዳንድ ያልገቡኝን ጥያቄዎች እጠይቃለሁ ።

፩ኛ/ በሀገራችን ባሉት ወህኒ ቤቶች አካባቢ ለሕግ እሥረኞች መጸለያ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው የሚገኘው ሌላ ታቦት እንዳይሠራ የሚከለከል አለ? ካለ ለኔና ለመሰል ጓደኞቼ ብትገልጹልን ፡

፪ኛ ጥር ፲ ፳ ፹፪ ዓ ም ገሃድ ጾም ነው ሥጋ አይበላም ተብሎ በአሁኑም ሆነ በተለያዩ ለአለፉት ዓመታት አልበላሁም ታድያ በተለመደው ሐሙስ ሥጋ እንዳይበላ ሲከለከል ዓርብ ሥጋ ተበልቷል ፈጽሞ አልገባኝምና ስለ ገሃድ በዝርዝር እንድትአስረዱኝ እጠይቃለሁ ።

፫ኛ/ በቁጥር ፩፻፵፰ የካቲትና የመጋቢት ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ትንሣኤ ገጽ ፬ ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቃለ ምዕዳን ሰጡ ይላል ። ይኸንን ቃል በየጊዜው እሰማለሁ ምዕዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንድታስረዱኝ በትህትና እጠይቃለሁ ። አይዞን ጋው ሳሙኤል መርዕድ

ከሰሜን ኦሞ አስ/አካባቢ
ዓርባ ምንጭ

መልስ

አይዞንጋው ሳሙኤል መርዕድ ስለአቀረብክልን መንፈሳዊ ሰላምታ እኛም በበኩላችን መንፈሳዊ ሰላምታ እናቀርብልሃለን ።

በመጀመሪያ ጥያቄህ በሀገራችን በሚገኙ ወህኒ ቤቶች ለሕግ እሥረኞች መጸለያ ከሚታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ከቅዱስ ሚካኤል ጽላት በስተቀር ሌላ የለም ይህ ለምን ይሆናል ? ስላልከው እንደአጋጣሚ አንተ ባታይ ይሆናል እንጂ የእመቤታችንም ሆነ የሌሎች ቅዱሳን ጽላት ቢሆን የሚከለክል ነገር የለም ለምሳሌ በጅማ ከተማ ላሉት የሕግ እሥረኞች መማፀኛና መጸለያ በታነፀችው ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጽላት ናት ። እንዲሁም በደሴ የመድኃኔ ዓለም ጽላት ነው መጸለያቸው ፡ ስለዚህ የቅዱስ ሚካኤል ጽላት ብቻ እንዲሆን አልተወሰነም እንዳጋጣሚ ካልሆነ በስተቀር ።

በሁለተኛው ጥያቄህ በጥምቀት ገሃድ ሐሙስ ሥጋ እንዳይበላ ተከልክሎ ዓርብ ሥጋ የተበላበት ምክንያት አልገባኝምና ግለጹልኝ የሚል ነው ።

በመሠረቱ ገሀድ ማለት ለውጥ ማለት ነው የልደትና የጥምቀት በዓላት ዓበይት ስለሆኑ በዋዜማው ተጾመው ዕለታቸው እንዲበላ ዓርብም ሆነ ረቡዕ እንዳይጾሙ በፍትሐ ነገሥት ስለተወሰነ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የአባቶቿን የሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንትን ውሳኔ በመከተል ታስተምራለች ትሠራለች ።

በሦስተኛው ጥያቄህ ላይ ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃለ ምዕዳን አሰሙ የሚል ቃል ሁልጊዜ ከትንሣኤ መጽሔት ማንበብክን ገልጸህ ትርጉሙ እንዴት ነው ብለሃል በግዕዝ ቋንቋ መዓደ መከረ ይልና ምዕዳን ምክር ይላል ። ስለዚህ ቃለ ምዕዳን ማለት የምክር ቃል ማለት ነው ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች
አዲስ አበባ ፡

በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ፀጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን እያልኩ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

ከዚህም በመቀጠል አንዳንድ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተገቢውን መልስ እንድትመልሱልኝ በፍጹም ልቡናዬ አምናለሁ የማቀርባቸውም ጥያቄዎች ፡

፩ኛ በወንጌል ውስጥ ብዙውን ጊዜ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንን ይጠቅሳል የእነዚህ ሃይማኖት ምንድር ነው? ልዩነታቸውስ እንዴት ነው ? —

፪ኛ በማቴዎስ ወንጌል ፲፩ ቁ ፲፩ ላይ ቅዱስ ዮሐንስ ከሁሉ የሚበልጥ ነቢይ እርሱ ነው ይልና በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጣል ይላል ምን ማለት እንደሆነ ስላልገባኝ እንድታስረዱኝ ፡

፫ኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሰ መቃብር ውስጥ ሶስት ቀን ሶስት ሌሊት ሰነበተ ይላል ። ግን አልሞላልኝ አለ ስለዚህ አብራርታችሁ እንድትገልጹልኝ ፡ ዛሬ ያቀረብኳቸው ጥያቄዎች የመጀመሪያዬ ጊዜ ስለሆነ መልሳቸውን እጠባበቃለሁ ?

ትንሣኤ መጽሔት በጣም አስፈላጊ ትምህርት የሚሰጥ ስለሆነ

(ወደ ገጽ ፫ ይዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# “ዘኢ.ይት—ዓወቅ ተከሥተ ወዘኢ.ይትረዓይ ተረእየ” የማይታወቅ ተገለጠ ታይቶ የማያውቅ ዕፁብ ድንቅ ተአምርም ታየ

በጥበበኞች ብልሃት በፈላስፎች ፍልስፍና ሊሠራ የማይችል ሥራ ሲፈጸም ዕፁብ ድንቅ ተአምር ይባላል ። ዕፁብ ከሚለው ቃል የሚበልጥ ሌላ ዓቢይ ቃል ስለሌለ ታላቅ ተአምር ተሠርቶ ሲታይ መልሶ መላልሶ ዕፁብ ድንቅ ተአምር ከማለት በስተቀር ሌላ ከዚህ የሚበልጥ ቃል ለማግኘት አይቻልም ፤ አንድ ደራሲ በቅኔው ይህንን ቃል ለማጉላመስ ፈልጐ የበለጠ ቃል ባለማግኘቱ “ዕፁብኬ ዕፁብ ውእቱ እስመ ለዕፁብ ትርጓሚ አልቦቱ” ብሏል ይህም ዕፁብ ያው ዕፁብ ነው ለዕፁብ ሌላ ትርጓሚ የለውም ማለት ነው ።

እግዚአብሔር አምላክ በሚወዳቸውና በሚወዱት ሰዎች ላይ እያደረ በየጊዜው ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደርጋል ። ተአምራቱም ቢጻፉ ሰማይና ምድር ወረቀትና ብራና ውቅያኖስ ቀለም ዕፀዋት ብዕሮች (እስኪርብቶች) ደቂቀ አዳምና መላእክት ጸሐፍት ሆነው ቢመዘገቡ እንኳን ባልተፈጸሙም ነበር ። ነገር ግን ጥቂቶቹ በጽሑፍ ተመዝግበው በየጊዜው የሚነሣውን ትውልድ ሲያስተምሩ ይኖራሉ ።

ከቀደሙትም ሆነ በቅርቡ ከተፈጸሙት ተአምራት አልፎን አልፎን ስመጥቀስ ለአንባብያን እናቀርባለን በዘመነ ኦሪት በሙሴ አማካይነት ብዙ ተአምራት ተፈጽመዋል ። ለምሳሌ አንድ ሰው በድምፅ ማጉሊያ ሲናገር ተናጋሪው ሰውዬው እንጂ መሣሪያው እንዳይደለ በአንድ ሰው አማካይነትም ተአምር ሲፈጸም እግዚአብሔር በሰው ላይ አድሮ ፈጸመው ይባላል እንጂ ሰውዬው እንደፈጸመው አይቆጠርም ።

፬፻፴ ዘመን በመከራና በሥቃይ የኖሩትን ሕዝበ እስራኤል ነፃ ለማውጣት እግዚአብሔር አምላክ ፈቃዱ ስለሆነ ሙሴን መርጦ ወደእነርሱ ላከው ፡ እርሱም አጅግ በጣም የሚያስደንቁ ተአምራትን በመሥራት ከምድረ ግብፅ አውጥቶ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ በደረቅ ያለምንም ችግር እንዲሻገሩ አደረጋቸው ጠላቶቻቸውም በኋላ ተከትለው ሊያጠቋቸው ሲሉ ሙሴ የተከፈለውን ባሕር በበትሩ ቢመታው እንደገና በመግጠም ጠላቶቻቸውን አስጥሟቸዋል ። ከዚያም በኋላ ውኃ ከደንጊያ እያፈለቀ መና ከሰማይ እያወረደ በተአምራት ፵ ዘመን መግቧቸዋል ይህንንም ነቢዩ ዳዊት ሲገልጽ ባሕርን ከፍሎ አሻገራቸው ውሆችን እንደ ክምር አቆመ ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ብርሃን መራቸው ዓለቱን በምድር ሰነጠቀ ከጥልቅ እንደሚገኝ ያህል በብዙ ውኃ አጠጣቸው ውኃን ከጭንጫ አወጣ እንደወንዞችም አፈሰሰ” ብሏል መዝ ፸፯ ፲፫ ፲፯ ።

እንዲሁም ነቢዩ ኤልያስ በዘመኑ የነበሩት ንጉሡ አክአብና ንግሥቲቱ ኤልዛቤል ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ አምላክ መታዘዛቸውን ቸል ብለው ለጣዖት ስለታዘዙ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ሰማይ ዝናምን እንዳያዘንም ፡ ምድርም የዘሩባትን እንዳታበቅል የተከሉባትን እንዳታጸድቅ አድርጓል ። ይህንን የመሰሉ ተአምራት ብዙ ተፈጽመዋል ። ሁሉንም ለመግለጽ ከላይ እንደተነገረው አይቻልም ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው በዘመነ ብሉይ የተፈጸሙ ናቸው ።

ወደ ዘመነ ሐዲስ መለስ ብለን የተመለከትንም እንደሆነ በየጊዜው የተፈጸሙትን ተአምራት ሁሉ ዕፁብ ድንቅ እያሉ ከማድነቅ በስተቀር ሌላ የምንጨምረው ነገር አይኖርም ፡ ቢሆንም ለማስታወስ ያህል በጥቂቱ እንመለከታለን ፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ከኃጢአት በስተቀር የሰው ልጆች የሚፈጽሙትን እየፈጸመ አድጓል ። በዚህ ዓለም ፴፫ ዓመት ከ፫ ወራት ኑሮ በመስቀል ላይ በመሰቀል የሰውን ልጆች ከፍዳና ከመርገም ነፃ ማውጣቱን ሁላችንም እናምናለን።

በዓለም ላይ እየተመላለሰ ያስተምርበት በነበረው ወቅት በቃና ዘገሊላ ሠርግ ተደርጎ ጌታችን ከእናቱ ድንግል ማርያምና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በዚሁ ሠርግ ቤት ተገኝተው ነበር ፡ ዕንግዳው ተጋብዞ ሳያበቃ ወይኑ አለቀ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወይን አልቀባቸዋል እኮ አለችው ማለቁ ለጌታ ተሠውሮት አይደለም ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ቀደም ተከተል ስላለው ጊዜው ገና ስላልደረሰ ነው እንጂ እመቤታችንም ለሁሉም የምሕረት አማላጅ የሰውን ደስታውን እንጂ ኀዘኑን ክብሩን እንጂ ውርደቱን የማትወድ ርኅርኅተ ልብ ናትና ።



በዚያ ፮ት የደንጊያ ጋኖች ነበሩ ውኃ ሙሏቸው ብሎ አሳላፊዎችን አዘዛቸው እነርሱም ሞሏቸው ጌታችንም ቀድታችሁ ስጡ አሊቸው ቀድተው ሰጡአቸው ዕንግዶቹም ወይኑን ቀምሰው አደነቁ የሠርጉንም ባለቤት ሰው ሁሉ ጥሩውን ወይም አስቀድሞ ያጠጣና መናኛውን በመጨረሻ ያጠጣል አንተ ግን የሚጣፍጠውን ጥሩውን ወይም አስቀድሞ የጠጣና መናኛውን በመጨረሻ ያጠጣል አንተ ግን የሚጣፍጠውን ጥሩውን ወይም እስከ አሁን አቆየህ አሉት ይህም ተአምር የመጀመሪያና ዓቢይ ተአምር ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ ተምዝግቧል ። ደቀ መዛሙርቱ የተደረገውን ተአምራት አይተው አምነዋል ።

እንዲሁም ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ፫፻፪ ዓ/ም በድንግል ማርያም ስም በፊልጵስዩስ የታነፀችው ቤተ ክርስቲያን ለመቀደስም ለቀድስትም ለቅኔ ማኅሌትም ለመሠረትም ለጣራም ፡ ለግድግዳም የበቁት ሦስት ደንጊያዎች መሆናቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል ። “በሠላስ አዕባን ገጸ ሥላሴሁ ለአምር ሐነፀ ቤትኪ ድንግል ድኅረ ፈጸመ ሣርሮ” ትርጓሚው ድንግል ሆይ ቤተ መቅደስሽን በሦስት ደንጊያዎች ሠርቶ ፈጸመ ይህም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያስረዳ ነው ማለት ነው ።

ቀደም ያሉትን ለማስታወስ ያህል መጥቀሳችን ነው እንጂ እግዚአብሔር በወዳጆቹ ስም በየጊዜው የሚፈጽመው ተአምር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ከመሄድ በስተቀር አልቀነሰም ርቀን ሳንሄድ በአዲስ አበባ ከተማ በእንጦጦ ኪዳነምሕረት በየካ ቅ/ሚካኤል በቡልቡላ አቦ ወዘተ ፀበል ጠጥተውና ተጠምቀው ከደዌ የተፈወሱትን ስንመለከት ፴፫ ዓመት ሙሉ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ኑሮ በክርስቶስ ቃል ከተፈወሰው በሽተኛ ያላነሰ ተአምር መፈጸሙን እንረዳለን ።

ነቢዩ ዳዊት “ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ” ምድር በመላዋ የእግዚአብሔር ናት ብሎ እንደተናገረው በማነኛውም ሀገር በማነኛውም ቦታ ለማነኛውም አማኝ የእግዚአብሔር ተአምር ይፈጸማል። ባለፈው ሰሞን ታይቶ የማይታወቅ ተአምር ታይቷል ተገልጾ የማይውቅም ነገር ተገልጿል ። በጆሮ ተሰምቶ የማይታወቅ ዜና በመገናኛ በራዲዮ ተነግሯል ፤ በጋዜጣም ተጽፎ ለአንባብያን ቀርቧል ።

ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ በአፍሪካም በአውሮፓም በእስያም እንዲሁም በሌሎች ዓለማት እየተገለጸች ለተማጸኑባት ወዳጆቿ ፍላጐታቸውን ለሟልታለች ። ግዳጃቸውንም ፈጽማላቸዋለች አሁንም እየፈጸመችላቸው ናት ።

ባለፈው ሰሞን በገብፅ ሀገር ፓርት ሰኢድ በምትባል ከተማ ወ/ሮ ሳሚያ ዮሴፍ ሆሲሊየስ ተብላ የምትጠራ የ፳፯ ዓመት ወይዘሮ የአንዲት ልጅ እናት የሆነች ጧት ማታ በቤተ ክርስቲያን እየተገኘች ትጸልይ ነበር ድንገት ከባድ በሽታ አደረባት ጸሎቷን ሳታቋርጥ ከተለያዩ ዶክተሮች ለበሽታዋ መድኃኒት ጠየቀች ። ነገር ግን ከዶክተሮች በሂደት ቁጥር የምትሰማው ቃል ሁሉ ወደሞት የሚጋብዝና ተስፋ የሚያስቆርጥ ቃል እንጂ የምሕረትና የድኅነት ዜና የሰማችበት ጊዜ ባለመኖሩ ሐኪሞቹን ርግፍ አድርጋ ትታ ወደድንግል ማርያም ተማፀነች ። እመቤታችን ድንግል ማርያምም በምሕረት እጇ ዳሳ ከሚያስጨንቃት ደዌ ሁሉ ከመቅጽበት ፈወሰቻት በመነሻው የማይታወቅ ተገለጠ ታይቶ የማያውቅ ዕፁብ ድንቅ ተአምርም ታየ ያልነውም ስለዚህ ነው ።

ቀድሞም ሆነ አሁን ወደፊትም አምላክ ለሚፈጽመው ተአምር የጊዜ ገደብ የተወሰነ ቦታ የለውም በእግዚአብሔር ስም አምነው መልካም ሥራ ለሚሠሩ ሁሉ ተአምር ይደረግላቸዋል ፡ ወንጌላዊው ማርቆስ ወያጸድቅ ነገሮሙ በተአምር ብዙኅ ብሎ እንደተናገረው በስሙ አምነው መልካም ሥራ ለሚሠሩ ሁሉ የሚሠሩትን መልካም ሥራ በተአምር ያስረዳላቸዋል ።

እንደገብፃዊቱ ወይዘሮ የሚያስጨንቅ ደዌ ያደረበት ሰው ቢኖር በእግዚአብሔር ስም አምኖ በድንግል ማርያም ይማፀን ፡ እመቤታችን በምሕረት እጇ በመዳሰስ ካደረበት ደዌ ተፈውሰዋለችና ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

በርቱ እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጣችሁ ፤

ከባሌ አስተዳደር አካባቢ አረና አውራጃ ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰን በት ት/ቤት የምገኘው ተማሪ ወርቁ ቸሬ

### መልስ

ተማሪ ወርቁ ቸሬ መንፈሳዊ ሰላምታን ከማቅረብህ ሌላ መጽሔቱን በመመልከት ጥያቄዎችን ስላቀረብክልን እናመሰግንሃለን ፡

፩ኛ/ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን የእግዚአብሔርን ህልውና በማመን አንድ ሲሆኑ የሚለያዩበት እምነት አላቸው ይኸውም ፤

(ወደ ገጽ ፲፬ የዞረ)



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስነታቸው በገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ የተሠራውን ሙዚየም ቤት መርቀው ከፈቱ የመሠረት ደንጊያ አስቀመጡ ፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አዲስ አበባ ከተማ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ደወል ቤት የተሠራውን የቅርሳቅርስ ማስቀመጫ ሙዚየም መርቀው የከፈቱት ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም ነው ።



ቅዱስነታቸው በሙዚየሙ መግቢያ የተዘረጋውን ጥብጣብ በመቀስ ሲቆርጡ

ቅዱስነታቸው በሙዚየሙ መግቢያ ላይ የተዘረጋውን ጥብጣብ በመቀስ ቆርጠው ለቅርሳቅርስ ማስቀመጫ የተሠሩትን ሽልፎች የዕቃዎችን አቀማመጥና አደራደር ለብዙ ዓመታት የተካበቱትን ንዋየተ ቅድሳት የንገሥታትን ልዩ ልዩ ስጦታዎችና የመዓርግ ዕቃዎች እየተዘዋወሩ አንድ በአንድ ተመልክተዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በጉብኝታቸው መጨረሻ በተዘጋጀው የክብር መዝገብ ላይ ቅዱሳዊ ፊርማቸውን አስቀምጠው በሰጡት መንፈሳዊ መመሪያ ይህንን ሙዚየም መርቀን ስንከፍት እጅግ በጣም ደስ ይለናል። ታሪክ አልፎ ታሪክ ሲተካ የሚያስመሰግነው ሰጭውን ብቻ ሳይሆን ጠብቆ ያቆየውንም በጣም ያስመሰግነዋል ። አባቶቻችን ጠብቀው ያቆዩን ቅርሶች የታሪካችን ፋናዎች ናቸው ማንኛውም ዕቃ ተመዝግቦ እንደዚህ በጥንቃቄና አስተማማኝ ባለው ቦታ የተቀመጠ እንደሆነ ለብዙ ዘመን ለመኖር ይችላል ክህነትና መንግሥትም ተጠብቀው የሚኖሩት በእነዚህ የክብር ዕቃዎች ነው እነዚህ ቅርሳቅርሶች ተጠብቀው እንዲኖሩ ለማድረግ በሥራም በአሳብም የደከማችሁትን ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ ብለው ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርቆሬዎስ በክብር መዝገቡ ላይ ፊርማቸውን ሲያስቀምጡ



ከዚያ ቀደም ሲል በዚሁ ዕለት ከጧቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ጥሪ የተደረገላቸው ካህናትና ምእመናን ለማረፊያ በተዘጋጀው ድንኳን የተመደበላቸውን ስፍራ ይዘዋል ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት የሰበካ ጉባኤና የልማትና የእድሳት ኮሚቴ አባላት የሰንበት ት/ቤት ተማሮች ከቤተ ክርስቲያኑ ወደ ሙዚየሙ በሚወስደው መንገድ ግራና ቀኝ ተሰልፈው የቅዱስነታቸውን መምጣት ይጠባበቁ ነበር ። ቅዱስነታቸው ከብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ጋር በመሆን የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ከቦታው በደረሱ ጊዜ በመዝሙር በጭብጨባና በልልታ ተቀብለዋቸዋል ። ሕፃናትም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ሊቀ ሥልጣናት ገብረ ማርያም ፈለቀ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እንኳን ደኅና መጡልን በማለት የመርሐ ግብሩን ቅደም ተከተል ገልጸዋል።

ቀጥሎም የተፈቀደላቸው ሦስት ሊቃውንት በየተራ ቅኔ አበርክተዋል ። ከዚያም የዕድገትና የልማት ኮሚቴ ሊቀ መንበር አቶ ወልደ አረጋዊ ።

ስለተሠራው ሙዚየም ጠቅላላ ይዞታና ስለጠየቀው ገንዘብና የሰው ኃይል ወደፊት ስለሚሰጠው አገልግሎት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል ። በመጨረሻም የለስላሳ መጠጥና የጣፋጭ ምግብ ግብዣ ተደርጓል ።



ሊቀ ሥልጣናት ገብረ/ማርያም ፈለቀ ሙዚየሙን ሲያስጐበኙ

## የመሠረት ደንጊያ ማስቀመጥ ፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ በከፍተኛ ፲፮ ቀበሌ ዜሮ ፪ ክልል ውስጥ በሁለት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ብር ለሚያሠራው የሕፃናት ማሳደጊያ ሕንፃ የመሠረት ደንጋይ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም አስቀምጠዋል ።

የምግባረ ሠናይ ሕጻናት ማሳደጊያ የሚል ስያሜን የተሰጠው ይህ ሕንፃ ፻፶፭ ሕፃናትን ሊይዝ የሚችል ባለ አንድ ፎቅ ሆስቴልና ከሕንፃው ጋር የተያያዘ አንድ ማዕከላዊ ክሊኒክ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች እንደሚኖሩት ታውቋል ።

ከተለያዩ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በተገኘው የገንዘብ እርዳታ የሚሠራው ሕንፃ በተለያየ የአስተዳደር ክልል ከሚገኙ የሕጻናት ማሳደጊያዎች ለከፍተኛ ትምህርትና ለተለያዩ የሙያ ሥልጠናዎች ወደ አዲስ አበባ ለሚላኩ ወጣቶች መኖሪያ እንደሚያገለግል ተገልጿል ። በአሁኑ ጊዜ በ፴፮ ሕጻናት ማሳደጊያዎች ፲፯ሺ፰፻፺፫ ሕፃናት መኖራቸው ተገልጿል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የመሠረቱን ደንጋይ ካስቀመጡ በኋላ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡ ለልማትና ለዕድገት ለብልጽግናና ለማኅበራዊ ኑሮ እንዲጣጣርና ኑሮውንም እንዲያሻሽል ትምህርቷን ከመለገስ ያቋረጠችበት ጊዜ የለም ብለዋል። ቅዱስነታቸው ቃለ ምዕዳቸውን በመቀጠል ትምህርት ለዕድገት ለብልጽግና ለማኅበራዊ ኑሮ ማሻሻያ ፍቱን መድኃኒት ነው ። በዚህ አዲስ በሚሠራው ት/ቤት የሚማሩም ልጆች ሀገራቸውን ወገናቸውን ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመርዳት ይችላሉ ። ይህንን የሚጀመረውን ሕንፃ እግዚአብሔር ለፍጻሜ ያብቃልን በማለት ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ሥነ ሥርዓቱ አብቅቷል ።

ከዚያ ቀደም ሲል ቅዱስነታቸው ከብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የወሎ ሀ/ ስብከተ ሊቀ ጳጳስ ጋር የዘዋር ተከታዎቻቸውን አስከትለው ከቦ



www.ethiopianorthodox.org

# ዓይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበ
# በግብጽ ፖርት ሰኢድ ከተማ የተከሰተ አስዳናቂ ተአምር

በተለያዩ የባሕር ማዶ ጋዜጦች አስገራሚ አስደናቂና ለማመን የሚያስቸግሩ ታሪኮች ይወጣሉ ። በብዕር ወዳጆች ድጋፍና ትብብር አንዳንዶቹ ይደርሱኛል ።

ሐኪሞችንና ሌሎች ባለሙያዎችን ላወያይና ልመካከርበት የሚገባ ጉዳይ እንጂ ሲገባ ይህንኑ ለማሟላት ላይ ታች እላለሁ ። ሲሟላልኝም ሳላውል ሳላሳድር "ለጥብስ" አደርሰዋለሁ ። ነገሩ የሚያስቆጣ ወይም በእንጀራዬ ላይ ነገር ቢጤ የሚያስቋጥርብኝ ከሆነ ግን "ጉመን በጤና" ብዬ መሳቢያ ውስጥ ክትት ነው ።

በዛሬው ዝግጅቴ የማቀርበው ተአምር የተባለለት ክስተት ግን ከማስገረምና ጉድ እስኪወዴያኛው ከማስባል በመለስ ጉራዴ ሊያማዝዝና የእንካ ስላንቲያ ጦር ሊያስብቅ የሚቻለው እንዳልሆነ ከወዲሁ እገምታለሁ ። እና እንደ ሌላው ጊዜ ለማመን የሚያስቸግሩ ታሪኮቼ የምሑር ሐኪምና የሊቀ ሊቃውንት ያለህ አላስባለኝም ። እንትልፍም አላጣሁበትም።

ባይሆን ወዳጄ ሲራጅ ሙሃመድ (በመንግሥት ምክር ቤት የጋዜጣና የትርጉም ዋና ኤክስ



ድንግል ማርያም ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም

ፐርት) የላኩልኝን የአስገራሚውን ታሪክ ፳፩ ገጽ ትርጉም መልሼ መላልሼ ማንበብ ነበረብኝ ። ታሪኩን በአንድ ዝግጅት እንዳላጠቃልለው በቦታው ጥበትና በመብዛትም አስለች ይሆናል ብዬ ሰጋሁ ላሳጥረው አስቤ ከላይ ከታች ከራስጌ ከግርጌ ቀንጫጩብኩት ። ዳሩ ግን መላ ቢስ ጉማዳ ሳይሆን ጉራዳ ሆኖ አገኘሁት ።

"ለምን ትለኛለህ አፍንጫ ጉራዳ

በልተህ አታውቅም ወይ የሸን ኮራ አገዳ"

ተብሎ የተገጠመው ትዝ ይበላችሁ ። በመጨረሻ ለአድማስ ወዳጆች ይስማማል ብዬ በገመትኩት መልክ አሰናድቼ በሁለት ተከታታይ ዝግጅቶች ላቀርበው ወደድኩ ። አስተያያታቸውን በመሣ.ቁ. ፫ ሺህ ፩፻፵፫ በስልክ ቁጥር ፲፩.፹፱.፰ እና ፲፩.፳.፵፩ ግለጹልኝ ።

በካይሮ ከተማ በየሳምንቱ እሁድ እየታተመ የሚወጣው "ወጠኔ" (አገሬ) የተባለ ታዋቂ ጋዜጣ በቅርቡ በቁጥር ፩ ሺህ ፬፸ እትሙ ለንባብ ያበቃው አንድ አስገራሚ ታሪክ ከብሔራዊ ክልል ባሻገር የብዙዎችን ትኩረት መሳቡ ይነገርለታል ። በፖርት ሰኢድ ከተማም ሆነ በድፍን ካይሮ ዋና የመነጋገሪያ ነጥብ ሆኖ የሰነበተውን አስደናቂ ክስተት ሌሎች ታዋቂ ጋዜጦችም ቢሆኑ ሳይዳሳሱት አላለፉም ።

ግብፃዊው ጋዜጠኛ ሙሰኢድ ጳዱቅ "በአሁኑ ጊዜ ሰው ሁሉ የሚነጋገርበት አስደናቂው ተአምር ከታማሚዋ ወይዞሮ አካል ላይ የነበረው ነቀርሳና እባጭ እንዴት ባለ ኦፕራሲዮን ጠፋ? ሕክምናውን ሲከታተሉ የቆዩት ሐኪሞችና የዓይን ምስክሮችስ ምን ይላሉ?" የሚለውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ያጠናቀረው ዘገባ በማርያም (ሥዕልና በሕመምተኛዋ ፎቶግራፍ ታጅቦ ለንባብ በቅቷል ።

ጋዜጣው (ጋዜጠኛው; ተአምር ታየበት ከተባለበት ሥፍራ በመሄድ ከተለያዩ የጉዳዩ ባለቤቶች ጋር ተገናኝቶ የተቀበለውን የዓይን ምስክሮች ቃልና ከሐኪሞች የተሰጠውን ማስረጃ አያይዞ ያቀረበው ሐተታ ትርጉም ቅንብር እንደሚከተለው ይነበባል ።

ቀዶ ሕክምና ለማድረግ ትዘጋጅ የነበረችው ታማሚ ወይዘሮ በድንገት የሳይንስ ሕግ በመጣስ ተአምር በዋዜማው ምሽት ከሕመምዋ ትፈወሳለች የሚል ዜና በመናፈሱ ሕዝቡ ወደ ከተማዋ እየጎረፈ በመሄድ ጸጥ ብላ የነበረችውን ከተማ አጨናንቋታል ። ይህን የመሰለውን አስደናቂ ተአምር ለማጣራትና ለመመርመር ወደ ሥፍራው መሄድ አስፈላጊ ሆኖ ታየን ። በዚህም መሠረት ወደ ፖርት ሰኢድ ከተማ ተጓዝን። ይህ ሁኔታ የፖርት ሰኢድን ከተማ ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሷል ።

አንዳንድ ጋዜጦች በመጀመሪያ ተአምሩን በጣም በተቆጠበ አመለካከት ጠቅሰው እንዲያውም ከዚህ አልፈው ሕልም ፡



ወ ሮ ሳሚያ የሴፍ ይህች ናት

የሃሳብ ጉዞና አሉባልታም የሚሉ ቃላትም ሰንዝረዋል ። በኋላ ግን ነገሩን በመረዳት ተጨባጩንና እውነቱን ተቀብለው አምነዋል ። የዚህንም ተአምር አስመልክተው ልዩ ትኩረት በመስጠት በሰፊው በዝርዝር ጽፈዋል ። በተለያዩ ዓለማት የሚገኙ የማስታወቂያ ተቋሞችም በሰፊው አብራርተዋል ።

ወይዘሮ ሣሚያ የሱፍ ፖሲሊየስ ትባላለች ። የሀያ ሰባት ዓመታት ዕድሜ ባለቤትና በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ሠራተኛ የሆኑ የሚስተር ፋኢቅ ሐና ባለቤት ናት ። የአንዲት ወጣት ተማሪም እናት ናት ። ወይዘሮ ሣሚያን የብፁዕ አቡቡሻወይ ቤተ ገዳምና ቤተ ክርስቲያን ካህናት ቤተ ክርስቲያንን አዘውታሪ ጸሎተኛ መሆንዋን ያውቃታል ። ጸሎተኛም ነበረች ።

"ከሁለት ዓመታት ጀምሮ የልብ ሕመም ይሰማኝ ነበር ። ነገር ግን በመጀመሪያው ምንም ዓይነት ትኩረትና ስሜት አልሰጠሁትም ነበር ። ነገር ግን ቀስ በቀስ በግራ ጡቴ ላይ እባጭ ተከሰተ ። እየዋለ እያደረ በመራባትና በመስፋፋት በብብቴ ስር እባጭ ታየ ። በዚህን ጊዜ ከቤተሰቦቼ ጋር በመሆን ወደ ተለያዩ ሐኪሞች በመሄድ በሽታውን በመከታተል የተለያዩ ምርመራዎችን ራጂዎችን እንዳደርግ አዘዙኝ ። የዚህ ምርመራ ውጤት እንደታየ ቤተሰቦቼ የበሽታውን አደገኛነትና ውጤቱንም ለመንገር ፈቃደኛ አልሆኑም ነበር ። እኔ ግን ጥርጣሬ አደረብኝ። ከፊቴም ላይ አደጋ እንዳለ ተሰማኝ ። ሐኪሞቹም በግራ ጡቴ ላይ ያለውን እባጭ በቀዶ ጥገና ማስወገድና ማጥፋት እንዳለባቸውና ግዴታም ጭምር መሆኑን ገለጡልኝ ። በዚህን ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ሥጋት አደረብኝ ። መድኃኒቱን እንዲልክልኝ ቅዱሳኖችንና ጻድቃኖችን ከመማጸን ሌላ አማራጭ ከፊቴ ባለመኖሩ ጸሎቴንና ሥግደቴን ቀጠልኩበት ተያያዝኩት ። እንዲያማልዱኝም መማጸኔን ከመቀጠል ወደኋላ አላልኩም። ከቅድስት ድንግል ሥዕል ፊት በመቆምና ወደቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመግባት እንባዬን እያጎረፍኩ በፊቷ ላይ ስግደቴንና መዋደቴን ተያያዝኩት በተጨማሪ ከሐኪሞችም ጋር የማደርገውን ምክርና ሕክምና በመቀጠል የተለያዩ ሀኪሞችን ከማየት አልተቆጠብኩም ። ከእነዚህም ሐኪሞች መካከል ።

---

ታው ሲደርሱ አቶ ፀጋዬ በርሄ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤት ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ድርጅት ኃላፊ ከድርጅቱ የቦርድ አባላት ጋር በመሆን ተቀብለዋቸዋል። ሕፃናትም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ። በተዘጋጀላቸውም መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ገለጻ ተደርጐላቸዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የቦታውን አቀማመጥ ግራና ቀኝ ተመልክተው ሊሻሻሉ ስለሚገባቸው ጉዳዮች መንፈሳዊ መመሪያ በመስጠት ወደ መንበረ ፓትረ ካናቸው ተመልሰዋል ።

ሊ.ኀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ





www.ethiopianorthodox.org

፩. ዶክተር ማኄር ሱለይማን ዘኪ ፡ የታንታ ከተማ የሕክምና ኮሌጅ ረዳት ፕሮፌሰርና የእባጭ በሽታ ባለሙያ ፡

፪. ዶክተር ነሽአት ሚካኤል የራጅ ባለሙያ.

፫. አጢፍ ኤልሰይድ ኤልባሕሪ፡

፬. ዶክተር ሻውቂ ሽሃታ አብዱልማሲ በፖርት ሰኢድ የሶሊዳሪቲ ሆስፒታል የቀዶ ሕክምና አማካሪ ይገኙበታል ።

"የመጀመሪያው ሐኪም ለእኔ ለእራሴ የቀዶ ሕክምና ከማድረግ ሌላ አማራጭ እንደሌለኝና ቆርጦ መጣሉም ግዴታ እንደሆነ በግልጽ አስረዳኝ ። ነገር ግን የእኔን ልብ ለማጽናናትና መንፈሴንም ለማረጋጋት ሲሉ አሁን የሚደረግልኝ የቀዶ ሕክምና ከእባጩ ዓይነት ናሙና ለመውሰድ ስለሆነ ምንም የሚያሰጋሽ ነገር የለበትም አሉኝ ። ዶክተር ሙሐመድ ዳውድ የተባሉት ሁለተኛው ሐኪም ደግሞ በበኩላቸው በልብሽ ላይ ትንሽ በሽታ አለ ፡ በሳምባሽ ላይ ያለው በሽታ በቀዶ ሕክምና ካልተነሳ ወደ ነቀርሳ ይለውጠዋል ብለን እንሰጋለን" አሉኝ ።

## ቀጠሮና ዝግጅት

ዶክተር ማኄር ሱለይማን ዘኪ የተባሉት የቀዳጅ ሃኪም (ሰርጂን) ለወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ ማክሰኞ ፌብርዋሪ ፳ ፲፱፻፹ ቀጠሮ በመስጠት የቀዶ ሕክምና ለማድረግ ወሰኑ ። ወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ በዚሁ የቀጠሮ ዕለት በካይሮ ሽብራ በተባለው ሰፈር አካባቢ በሚገኘው ክሊኒካቸው እንዲገኙና የቀዶ ጥገናው ሕክምና የሚካሄድ መሆኑን ገለጹላት ።

ወይዘሮ ማሚያ ከቀጠሮው ቀን በፊት ባለችው ሌሊት ማልዶ ለመነሳትና ወደ ካይሮ ጉዞዋን ለመቀጠል እንድትችል ፖርት ሰኢድ ከተማ በቁስ ፖላ ሰኢድ ቤት አዳሯን ወሰነች ።

## የዓይን ምስክሮች

የካህኑ ባለቤት ወይዘሮ ናስኔ አሚራ ሰላማ ወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ ወደ ቤታችን ከገባችበት ሰዓት ጀምሮ እኔ አልተለየሁዋትም ። ወደቤታችን የመጣችው ባለፈው ሰኞ ማታ ለአራት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ላይ ነበር ። በሁለተኛው ቀን የሚካሄደው ቀዶ ሕክምና በጣም ያስደነገጣትና ያሰጋት መሆኑም ከፊቷ ላይ ይነበብ ነበር። እኔም በበኩሌ ማፅናናት ጀመርኩ ። ወይዘሮ ማሚያም በንግግራችን መካከል ጣልቃ በመግባት ከዚህ በታች ያለውን ጥያቄ አቀረበችልኝ ።

ብፁዕ አባታችን እንዳሉት በተአምር እኔ ለመዳን እችላለሁን? አለችኝ ። እኔም በበኩሌ ፈጣሪያችን ሁሉን ነገር ለሚያደርግ ችሎታ አለውና ሊያደርግ ይቻላል አልኩዋት ። ከዚህ በኋላ ወይዘሮ ማሚያ በቤታችሁ ውስጥ በንጥረ ነገር የተመጠነ ጢስ ሸተተኝ አለችኝ ። እኔም በበኩሌ ጉንፋን ስለያዘኝ ለእኔ አልሸተተኝም ብዬ መለስኩላት ። እንደገና ከምሽቱ በፈረንጅ አቆጣጠር በአሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ አበና በላ ሙሊድ ባለቤቴ ወደቤት ሲመለሱ የሰማሁትንና ያየሁትን ገለጽኩላቸው። የጢሱንም ጉዳይ አንስቼ ነገርኩአቸው ። አቡናም በበኩላቸው አንዳንድ ገዜ ይህን የመሰለው ሁኔታ የሚከሠተው በብዛት የተአምር መቅደስም ስለሚሆን ነው አሉኝ ።

ለወ/ሮ ማሚያ ልዩ ክፍል አዘጋጅተንላት ስለነበር ወደመኝታ ቤቷ ገብታ ስትተኛ ከአጠገቧ ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንና ከቅዱስ አባኖብ ሽኖዳ ቅባ ቅዱስና ዘይት የተነከረ ፎጣና ጥጥ የያዘ ሶስት ትናንሽ ኪሶች ወስጄ ሰጠሁዋት ። እርስዋም በበኩሏ ከትራሱ ሥር አስቀመጠችው ይህ ሁሉ ሁኔታ የተፈጸመው በእኩለ ሌሊት በአሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ነበር ።

ከዚህ በኋላስ ምን ተፈጸመ? አስገራሚና አስደናቂ የሆነውን ክስተት ረኩ ባለቤት ወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ ፖሲሊዮስ ከሁለት ዓመታት ወዲህ የልብ ሕመም እየተሰማት ይቆይና ቀስ በቀስ በግራ ጡትዋ አካባቢ እባጭ ይወጣል ። በሽታው አደገኛ በመሆኑ እባጩን በቀዶ ሕክምና ለማስወገድ የካይሮ ሐኪሞች ይወስናሉ ፌብርዋሪ ፳ ቀን ፲፱፻፹ ማክሰኞ ወይዘሮዋ ለኦፕራሲዮን ካይሮ መሄድ ነበረባት ። ወ ሮ ማሚያ ማለዳ ለመነሳትና ለጉዞዋ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በዋዜማው ሰኞ ዕለት ፖርት ሰኢድ ከተማ በቁስ ፖላ ሰኢድ ቤት አዳሯን ለማድረግ ወሰናለች ። ሕመምተኛዋ ወ ሮ ማሚያ ቁስ ፖላ ቤት ስትደርስ የቁሱ ባለቤት ተቀብለው ተገቢውን መስተንግዶ ካደረጉላቸው በኋላ የመኝታ ክፍልም ይሰጡአቸዋል ። ምሽት ላይ ቁስና ባለቤት ወደ መደበኛው ወይዘሮ ማሚያ ደግሞ ወደተዘጋጀላቸው የእንግዳ ማረፊያ ክፍል ይገባሉ ። እስከዚህ ያለውን ተጨዋውተን ነበር ሳምንት የተለያየነው ።



## ከዚህ በኋላ ምን ሆነ?

ከእኩለ ሌሊት በኋላ በአንድ ሰዓት ላይ (በኢትዮጵያውያን የሰዓት አቆጣጠር ከሌሊቱ ፯ ሰዓት) ወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ ከተኛችበት ክፍል እህ!እህ! አይ!አይ! የሚል ድምፅ ሰማሁ ። ከዚያም "ይሰማኛል! ይሰማኛል! የሚል ድምፅ ከአ...እታ ጋር ተሰማኝ ። ይህንንም በተደጋጋሚ በሰሙ ጊዜ ቁስ ፖላ ከእንቅልፋቸው ተነስተው ወደ ወይዘሮ ማሚያ መኝታ ቤት ገብቼ እንዳያት ጠየቁኝ ። እኔም ክፍሏ ገብቼ በአየሁዋት ወቅት በአልጋዋ ላይ ተኝታ አገኘሁዋት። ያየሁት ሁኔታ በጣም አስደነገጠኝ ። ለብሳው የነበረው ሹራብ በደም ተነክሯል ። እንደ እባጭ የተድቦለቦለና ከሰውነቷ የወጣ ቁራጭ ሥጋ በአጠገቧ ተበታትና አየሁት ። ይህ ሁሉ ሲሆን እርስዋ በእንቅልፍ ላይ ናት ። ጨኽቷና እህታዋ ለእኔ ይሰማኛል ። ማቃሰቷን አላቋረጠችም ነበር ።

ጠራሁዋት ። በጣም ደክም ባለ ድምፅ አንቺ ማነሽ በማለት መልስ ሰጠችኝ ። አሚራ ነኝ በማለት መለስኩላት ። ነገር ግን ተመልሳ በሰመመን የእንቅልፍ ባሕር ሰጠመች ።

ይህን ያየሁትን ነገር ሁሉ ለባለቤቴ ለቁስ ፖላ በዝርዝር አስረዳሁዋቸው ። በሰውነቷ ላይ ያየሁት ሁሉ በጣም የሚያስገርም ነው ። ደሙ ሰውነቷን አዳርሶ ሸፍኖታል። በተለይም በግራ ጡቷና ደረቷ በሙሉ በደም ተሸፍኗል አልኩአቸው ። ቁስ ፖላ ወደ ክፍሏ ገቡና ማሚያ ምን ሆንሽ? ብለው ጠየቋት አሁንም መልስ አልሰጠቻቸውም ይህም በመሆኑ መጥፎ ነገር ደርሶበታል ብሰ/በሥጋት ላይ ወደቅን ። ከእኩለ ሌሊት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ገደማ ላይ ስትስል ድምፅ ሰማሁ ። በሕይወት እንዳለች በማወቴ ተመስገን አምላኬ ሆይ በማለት ለፈጣሪያችን መስጋናዬን አቀረብኩ ።

ጠዋት ለአሥራ ሁለት ሩብ ጉዳይ ላይ ቁስ ፖላ ወይዘሮ ማሚያ ክፍል ገብተው እንደምን አድርሽ ብለው ሲጠይቋት የሰጠቻቸው ፡ መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር ። "እኔ በዛሬዋ ሌሊት ቅድስት ድንግል ከዚህ ከጐኔ ቁጭ ብላ አየሁዋት ። የመጣሁትም ለአንቺ የቀዶ ሕክምና ላደርግልሽ ነው አለችኝ ። አንድ ወጣት ልጅ ነጭ ቀሚስ የለበሰና ሁለት ክንፍ ያለው አንድ አዛውንት እንዲት ነጭ ቀሚስ የለበሰች አሮጊት ሴት አብረዋት ነበሩ ። ከሁለት ቀን በፊትም አይቻት ስለነበር በዚያም ጊዜ አይዞሽ ስለ ኦፕራሲዮን አትፍሪ ፡ ኦፕራሲዮኑን እኔ ነኝ የማደርግልሽ ብላ ነግራኝ ነበር ። ይኸውና አሁን ቤቃ በልቤ ላይ ያለው ሁሉ ተነሳልኝ" ስትል ለቁስ ፖላ ገለጸችላቸው ። እኔም ከቁስ ፖላ ጐንና ከወይዘሮ ማሚያ ፊት ቆሜ እንደ ተመለከትኩት የወይዘሮ ማሚያ እጆችና እንዲሁ ሹራቧ በደም የተነከሩ መሆናቸው በጉልህ ይታዩ ነበር ። እንደዚሁም ራስዋ ወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ ቁርጥራጭ ሥጋ በደም የተለወሱት እጆችዋንና ሰውነቷ ላይ የነበሩ ልብሶች ሁሉ በደም ርሰው በአየችበት ወቅት" ምንድን ነው ይህ አስጸያፊ ነገር? ልብሶቹ ሁሉ ንጹሕ ነበሩ አሁን ተነስቼ ልብሶቹን ማጠብ አለብኝ አለችን ። እኛም በበኩላችን ልብሶቹ እንዳሉ ተቀምጠው እርስዋ ግን ወደ መጸዳጃ ቤት ገብታ መታጠብ እንዳለባት ጠየቅናት ።

ወደ ባኞ በገባችበት ወቅትም ሐኪም ከደረቷ ላይ አስሮት የነበረውን ሻሽ ስትፈታው ታስሮ የነበረው እባጭ በመጥፋቱ ማሰሪያው ላልቶ አገኘችው ። ከእባጩ ተቆራርጦ የወደቀ ሥጋ አገኘች ። እነዚህን ያገኘቻቸውን ነገሮች ሁሉ በወረቀት ኪስ አስቀመጠች። በደም የተለወሱትን ልብሶች ፡ ጡት መያዣና ጡቷ የታሰረበትን ሻሽ በጥንቃቄ አስቀመጠችው" ሲሉ ወይዘሮ አሚራ ገልጸዋል ።

ወይዘሮ ማሚያ በሰመመን ላይ በቆየችበት ወቅት የታያትን መንፈሳዊ ክስተት እንድታስረዳ ተጠይቃ "ከተከሰቱልኝ መንፈሳውያን ክስተቶች መካከል አንዱ ቅድስት ማርያም በዘይቱን በምትገኘው ቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ተከስታ በታየችበት ወቅት እጅዋን ዘርግታ ስትጸልይ እንደታየችው ልክ በዚያው ሥዕል መልክ አየሁዋት ። ሌላው ሥዕል ደግሞ በእንባ ቡሻወይ ሥዕል የተመሰለ የአንድ አዛውንት ምስል ሲሆን አንድ ሕፃን ልጅ በቅዱስ አባኖብ ተመስሎ ተከስተውልኛል ።" ስትል ገልጣለች ።

## ከጳጳሱ ጋር የተካሔደ ውይይት

ጋዜጠኛው ወደ ቦታው በሄደበት ወቅት በፖርት ሰኢድ ጳጳስ ከብፁዕ አባ ቴዎድሮስ ጋር በአደረገው ውይይት ፡ የታየውን ተአምር ብፁዕነታቸው በራሳቸው የተመለከቱት መሆናቸውን ገልጸው ይህን ሁኔታ በቴሌፎን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሽኖዳ ፫ኛ



www.ethiopianorthodox.org

በግብጽ የአልክሳንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የገለፁላቸው መሆናቸውን አስረድተዋል ።

ብፁዕ አቡነ ሽኖዳ ፫ኛ ሁኔታው በዝርዝር ሲነገራቸው የታዩት የተአምር ምልክቶች ሁሉ በዝርዝርና በጥንቃቄ ተጠብቀው ከዝርዝር ሪፖርት ጋር እንዲላክላቸው ጠይቀዋል ሲሉ በፖርት ሰኢድ የሚገኙት ጳጳስ መናገራቸውን ጋዜጣው ጠቅሶአል ።

## ከካህኑ አንደበት

ተአምሩ በተከሰተበተ ሌሊት ወይዘሮ ማሚያ የአደረችበትን ቤት ባለቤት ቄስ ፖላን ለመጠየቅ ጋዜጠኛው ወደ ቦታው ሄዶ ነበር። ቄስ ፖላና ሙሰኢድ በበኩላቸው ከሰጡት መልስ ባለቤታቸው ወይዞሮ የሰኔ አሚራ ሰላማ የሰጡትን የዓይን ምስክርነት ያረጋገጡ ሲሆን በተጨማሪም ራሳቸው በግል የተመለከቱትንና ከተአምሩ ባለቤት ከወይዘሮ ማሚያ ዩሱፍ ጋር ያደረጉትን ውይይት ጨምረው አብራርተዋል ።

## ሕክምናውን ሲከታተሉ የቆዩት ሐኪም

ሕክምናውን ሲያካሂዱት የቆዩት የእባጭና የቀዶ ሕክምና ባለሙያ ዶክተር ሣሂር ሱለይማን ዘኪ ሲሆኑ ጋዜጠኛው ከዶክተሩ ጋር ተገናኝቶ ተወያይቷል ።"የወይዘሮ ማሚያን በሽታ ስከታተለው ነበር ። በዚህም መሠረት የተነሳችው ራጅና ልዩ ልዩ የላብራቶር ምርመራ ላይ በሳምባዋ የአየር መተላለፊያ ቧምቧ ሽፋን ላይ ለውጦች መገኘታቸውን ውጤቱ አረጋግጦአል ። ይህም ሁኔታ ነቀርሳ ከመሆኑ በፊት ያለውን ደረጃ የሚገልጽ ሲሆን እዚህ ላይ በተጨማሪም በግራ ጡቷ ላይ እባጭ የተከሰተ መሆኑን አረጋግጦአል ። እነዚህ ነገሮችም የነቀርሳን ክስተት የሚያረጋግጡ ናቸው።

እኔ በተአምሩና ተአምሩም ከተከሰተ በኋላ እባጩ የተወገደና የጠፋ ለመሆኑ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ የለኝም ። ሁኔታውን ለማረጋገጥ አሁን በየዝነው ወር በፌብሪዋሪ ፳፭ ቀን ፲፱፻፹ ለወ/ሮ ሣሚያ እንደገና በተደረገላት አዲስ ምርመራ ሳምባዋም ሆነ ሌላው መቶ በመቶ ንጹሕ መሆኑ ተረጋግጦልናል ። በሳምባዋ ላይም ሆነ በውስጥ ምንም ዓይነት የኢንፌክሽን ቁስልም ሆነ ሌላ ለውጥ የለባትም ። ግራ ጡትዋ ከዚህ እባጭ መቶ በመቶ ነጻ መሆኑን አረጋግጠናል ቀደም ሲልም ከብብትዋ በታች የነበረው እባጭ ሁሉ ጠፍቶ አካባቢው ከማንኛውም የእብጠት ምልክት ሁሉ ነፃ መሆኑን አረጋግጠናል" ሲሉ የሕክምናው ባለሙያ ዶክተር ሣሂር አረጋግጠዋል ።

ዶክተር ሣሂር ሱለይማን ይህ ተአምር በታየበት ወቅት በሽተኛዋ ወ/ሮ ለብሰውት የነበረውንና በደም የቀለመውን ልብስ እንዲሁም በብልቃጥ የተቀመጠውን ቁርጥራጭ ሥጋ በዓይናቸው ተመልክተዋል ።

## በሌሎች ሐኪሞች ትዝብት

ሰሞኑን በግብፁ ውስጥ በፖርት ሰኢድ ከተማ የተከሰተውና ሰውን ሁሉ በየቦታው ሲያነጋግረው የቆየው ተአምር በዚህ ብቻ አልተገታም ። ሌሎችን የተለያዩ ሐኪሞችንም ጭምር የሳበና ዕውነቱን ለማወቅ ያሯሯጠ ጉዳይ ነበር ።

በዚህም መሠረት በደም የተለወሰው የሴትዮዋ ልብስና የተቆራረጠው ሥጋ ፖርት ሰኢድ ወደም ትገኘው ቅድስት ማርያም ቤተ ብርስቲያንና ወደ ብፁዕ አባ እንባ ቡሻወይ በተወሰደበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ የተለያዩ ሐኪሞች ተሰብስበው ሁኔታውን ተመልክተውታል ። ከእነዚህም ሐኪሞች መካከል የቀዶ ሕክመና ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ሻውቅ አብዱል መሲህ ዶክተር ሙራድ ዘኪ ፣ ዶክተር ጠልአት መክረ የቀዶ ሕክምና ባለሙያ ፣ ዶክተር ላይላ ሹክሪና ዶክተር ዑሣማህ ፋኦድ ይገኙበታል ።

በፖርት ሰኢድ ከተማ የተከሰተው ተአምርና ዜናው ወደ ካይሮ በመዛመቱ ትኩረታችንን ካይሮ ላይ አድርገናል ። ተጨማሪውንና ዝርዝር ሁኔታውን በመጭው ሳምንት እንመለከተዋለን በማለት የግብፁን ጋዜጠኛ ከመሰነባበታችን በፊት

በግብፁ ፖርት ሰኢድ ከተማ የተከሰተውን ተምር የሚያብራራውን ጽሑፍ ሙሉ ትርጉምና ጋዜጣውን ለሰጡኝ ተከታዩንም እንደ ማይነፍጉኝ ለምንተማመንባቸው ለጓድ ሲራጅ ሙሐመድ ኢብራሂም እንዲሁም ለሙያ ባልደረባዬ አሰፋ ስዩም ለተሳትፎአቸው ምሥጋና አቀርባለሁ ።

ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ
መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም

I

# በአዲስ አበባ ሀ/ስብከት ፺ ካህናት ተመረቁ

ከኅዳር ወር ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ፲፰ ቀን ፹፪ ድረስ በተከታታይ ለስድስት ወራት የሠለጠኑ ፺ ካህናት ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም በጠቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አዳራሽ የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተገኝተው የምስክር ወረቀቱን የሰጡትም ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ናቸው ። ከአንድ እስከ ሦስት ለወጡትም ልዩ ልዩ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል ሽልማቱንም የሰጡት ዶ. ማርቆስ ወልደ ኢየሱስ የጠቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው ዶክተር ማርቆስ ሽልማቱን ከሰጡ በኋላ ባደረጉት ንግግር "የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት ተምረዋል አውቀዋል ። ሠልጥነዋል ይላል እንጂ አስተምረዋል አሠልጥነዋል አይልምና ወደፊት በተማራችሁት በርትታችሁ ሥሩ በዚህ ማሠልጠኛ በቆያችሁበት ጊዜ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ተምራችኋል ግን መሥራትና ማገልገል የምትችሉት እንደተሰጧችሁ ነው እንጂ ያለ ችሎታችሁ ተመድባችሁ ሥሩ አትባሉም የአንዱ ልምድ ለሌላው ትምህርት ነው በተቀበላችሁት ዕውቀት አሁንም በርትታችሁ ሥሩ" በማለት መመሪያ ሰጥተዋቸዋል ።

ከዚህ ቀደም ሲል የማሠልጠኛው ኃላፊ መ/ገብረ እግዚአብሔር ማኅፀንቱ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

የመ/ ገብረ እግዚአብሔር ማኅፀንቱ ንግግር

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፣

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቅዱስነታቸው ረዳት ሊቀ ጳጳስ

ክቡር ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አሥኪያጅ

የመምሪያ ኃላፊዎችና የማሠልጠኛው መምህራን ፣

የገዳማትና የአድባራት አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች፣ እንዲሁም ጥሪያችንን አክብራችሁ የመጣችሁ እንግዶች ፣ እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ካህናት ማሠልጠኛ ት ቤት ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።



ዶ. ማርቆስ ወ ኢየሱስ ሽልማት ሲሰጡ

በዛሬው ዕለት የምረቃ በዓሉን በተመለከተ አጭር መግለጫ እንዳቀርብ እንዲፈቀልኝ ስጠይቅ ከፍ ባለ አክብሮትና ትህትና ነው።

## ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ሆይ!

ይህ ማሠልጠኛ በቅዱስነትዎ በዓለ ሢመት ማግሥት በጥቅምት ወር መጀመሪያ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም በቅዱስነትዎ ጸሎትና ቡራኬ ተከፍቶ ሥራውን ከጀመረ ፪ኛ ዓመቱን በማገባደድ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዛሬው ዕለት የ፬ኛውንና የ፭ኛውን ዙር ፺ ካህናትን ለማስመረቅ ቀርበናል ።

## ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ሆይ!

እንደሚታወቀው ሁሉ በማሠልጠኛው በአሁኑ ጊዜ የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ፲፫ ሲሆኑ የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ከ፪ ሰዓት እስከ ፰ ሰዓት ተኩል ነው ።

የመምህራኑም ብዛት ፲፪ ናቸው ።

የትምህርቱም አሰጣጥ በየጊዜው እየተሻሻለ መምጣቱን ልገልጽ እወዳለሁ ።

ይህም ሊሆን የቻለው መምህራኑ በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ የትምህርቱን አሰጣጥ በተመለከተ ስብሰባ ስለሚያደርጉና በተለይም የመምህራንና የተማሮች አጠቃላይ የጋራ ስብሰባ ውይይት እንዲኖርና አንድ አንድ እርምት ከመደረጉ የተነሣ ነው የእያንዳንዱ መምህር የትምህርት ዝግጅት በሽት እየተባዛ ለሠልጣኞች ካህናት በመታደል ትምህርቱ በጥራትና በብቃት መካሄዱን ያመለክታል ። ለጥናትም አመች ሁኔታን ፈጥሮአል ።

ማሠልጠኛው ሥራውን ከጀመ

፲፩

www.ethiopianorthodox.org

ረበት ቀን ከ፩ኛው ዙር እስከ ፳ኛው ዙር በጠቅላላው ተመርቀው የወጡት የካህናት ብዛት ፲፱፻፳፱ ደርሷል የ፳ኛውም ዙር ሥልጠና ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ ም



በ፲ኛ ዙር ፩ኛ የወጣው አዳሙ አምሩ

ይጀመራል ።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሥልጥነው ከወጡት ፲፱፻፳፱ ካህናት መካከል ብዙዎቹ በየደብራቸው በሥለጠኑበት የሥራ መስክ ተሠማርተው ቀደም ሲል ያካበቱትን ዕውቀት በስልጠናው ወቅት ካገኙት ፡ ትምህርት ጋር በማዋኸድ



በ፲ኛ ዙር ፪ኛ የወጡት መ ጋቤ ተስፋ ፍሥሐ

በትጋትና በቅንነት እየሠሩ መሆናቸውንና እኛም እንደተከታተልነው ከአንዳንድ የአብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ ጽ ቤት ሪፖርት እየደረሰን ነው ።

ይህም የሥራ እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቲያናችንን ዕድገትና የሰበካ ጉባኤን መሻሻል ያመለክታል ።

## ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ!

ማሰልጠኛው ሊሻሻል የቻለውም በቅዱስነትዎ መልካም ፈቃድና አርቆ አስተዋይነት መጀመሪያ ማሠልጠኛው በገንዘብና በተማረ የሰው ኃይል ተሟልቶና ተደራጅቶ በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ እንዲከፈትና ሥራው በተሟላ ሁኔታ እንዲካሄድ በመፈቀዱ ነው ።

በተጨማሪም ቅዱስነትዎ ብዙ የተደራረበና አስቸኳይ ሥራዎች እያሉብዎ ደከመኝ ፡ ሰለቸኝ ልረፍ ሳይሉ ፡ ከማሠልጠኛው የትምህርት መስጫ ክፍል በየጊዜው በመገናኘትና የሥራ መመሪያም በመስጠት ፡ የሠልጣኞችን አእምሮ የሚያድሱና የሚያተጉ የሚያነቃቁም የትምህርት ዓይነቶችን በጥያቄና መልስ መልክ በማዘጋጀት ፡ በሽት እየታተሙና እየተባዙ ለሠልጣኞች ከመታደላቸው የተነሣ ለማሠልጠኛውም መምህራንም ሆነ ለተማሪዎች እንዲሁም ለሠራተኞች ማበረታቻ የሞራል ድጋፍ ሆኖናል ።

በዚህም አጋጣሚ የዛሬዎቹ ተመራቂዎች ደስ ሊላችሁ ይገባል ።

በመጨረሻም ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ያላቸውን የተከማቸና የዳበረ ዕውቀት በማካፈል ለደከሙት የማሠልጠኛው መምህራንና እንዲሁም የትምህርቱን ፕሮግራም ተፈጻሚነት እንዲኖረው ለደከሙት ሠራተኞችና በተለይም የመማሪያ ክፍሉንና የተጓደለውን ሁሉ በማሟላት የተባበሩንን የገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ሰበካ ጉባኤ ጽ ቤትና የደብሩን አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት ገ/ማርያም ፈለቀን በማሰልጠኛው ስም ምስጋናየን አቀርባለሁ በማለት መ ገብረ እግዚአብሔር ማኅፀንቱ ንግግራቸውን አጠቃልለዋል ።

ከሠልጣኞችም መካከል የተፈቀደላቸው ሦስት ካህናት ቅኔ ሲያበረክቱ እንዲሁም ሌሎች ያሬዳዊ ዜማ አሰምተዋል ።

ሊ.ቀ.ኅ. ልሣኑ በዛብኅ

---

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፫ የዞረ)

ፈሪሳውያን ሙታን እንደሚነሡ ያምናሉ ነገር ግን ከትንሣኤ በኋላ ሚስት አግብተን እንኖራለን ይላሉ ፡ ሰዱቃውያን ግን ሰው ከሞተ በኋላ ፈርሶ በስብሶ ይቀራል እንጂ ፈጽሞ አይነሣም ባዮች ናቸው ። ልዩነታቸው ባጭሩ ይኸው ነው ።

፪ኛ በማቴዎስ ወንጌል ፲፩ ፲፩ ያቀረብከው ጥያቄ

ቅዱስ ዮሐንስ ገና ሳይወለድና ከእናቱ ማኅፀን ሳይወጣ ከዊቱተ ነቢያት አንዱ ነቢዩ ሚልክያስ "እነሆ በፊት በፊት እየሄደ መንገድን የሚጠርግ ወይም የሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን ካንተ በፊት እልካለሁ ብሎ ትንቢት ተናግሮለት የተወለደ እንደዚሁም የዓለምን መድኅን ክርስቶስን ያጠመቀ ዓቢይ ነቢይ በመሆኑ ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ የሚበልጠው የለም ተብሎዋል ፡ ነገር ግን በልደተ ሥጋ የሚያንሰው ይበልጠዋል የተባለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለማስገባት ሥልጣን አለውና ።

ሦስተኛው ጥያቄ ግን በትንሣኤ መጽሔት ቁ. ፩፻፹፩ ተብራርቶ የተሰጠ መልስ ስላለ ያንን ተመልከት ።

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## ሽ/ኮፕቶች በዐረብ አገዛዝ ሥር ።

(፩) ዐረቦች በግብጽ የነበረውን የቤዛንታይንን ጦር ድል አድርገው መግዛት ።

በግብጽ ቀደም ሲል በሮም ፡ ቀጥሎም በቤዛንታይን መንግሥታት ተይዛ በመገዛት የስንዴ ማምረቻና በጣም ሀብት የሞላባት ሀገር ነበረች ።

በየጊዜው ለንግድ ተግባር ሸቀጣ ሸቀጣቸውን በግመሎቻቸው እየጫኑ በእስክንድርያ በኩል ይተላለፉ የነበሩ የእስላም (የዐረብ) ነጋዴዎች በሀገሪቱ ከፍተኛ ሀብት ይጐመጁ ነበር ። ሀገሪቱን በሚገባ ከተመለከቷትም (ከሰለሏትም) አንዱ በ፮፻፴፱ ዓ/ም እዚያ የነበረው የቤዛንታይን ሠራዊት ደምስሶ ግብጽን የያዘው የከሊፋ ዑመር (፮፻፴፬—፮፻፵፬) ጀኔራል የነበረም አምር ኢብን አል አስ ነበር አምር በዚያን ጊዜ መዲና ከነበረው ከዐረቦች ገዥ ከከሊፋ ኡመር ትእዛዝ በመቀበል ፈረሰኛና እግረኛ ሠራዊቱን አሰልፎ ግብጽ ከነበረው ከቤዛንታይን ሠራዊት ጋር ከሁለት ዓመት በላይ ከተዋጋ በኋላ በ፮፻፵፪ ዓ/ም መላ ግብጽን ያዘ ። ወዲያውም ብዙ መጻሕፍት የነበሩበትን ታላቁን የፕቶሎማይክ ቤተ መጻሐፍት ዘመባል በዓለም የታወቀውን የእስክንርያ ቤተ መጻሕፍት ፡ በውስጡ የተከማቹት መጻሕፍት ይዞታ ለቁራን ትምህርት ተቃራኒ ነው በሚል ሰበብ አቃጠለው።

በዚሁ ጦርነት ወቅት ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ኮፕቶች በቤዛንታይን ገዥዎቻችው የተፈጸመባቸውን ገደብ የለሽ ግፍ በማስታወስ ጦርነቱን በግድየለሽነት ከመመልከት በስተቅር ለቤዛንታይን ሠራዊት ምንም ዐይነት እርዳታ አላደረጉም ።

ዐረቦች ግብጽን ለመያዝ ሲቃረቡ የሀገሪቱ ዜጎች (ኑእሪ) የነበሩት ኮፕቶች ፡ መለካውያንና አይሁዶች ከሚከተሉት ሦስት ጥያቄዎች (ግዴታዎች) አንዱን በመምረጥ በተግባር እንዲያውሉ ጠየቁአቸው ። ጥያቄዎቻቸው የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ) የእስልምናን እምነት ተቀብሎ ከአማኞች (ከእስላሞች) ጋር መቀላቀል ፡

፪ኛ) ያለምንም ድርድር የዐረቦችን ድል አድራጊነትና ገዥነት ተቀብሎ መንግሥት የሚወስነውን እንደ እስላሞች ከሚበፈለው ሕጋዊ ከሆነው መደበኛ ግብር በተጨማሪ ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን ብቻ የሚመለከተውን የነፍስ ወከፍ (የግንባር) ግብር ጭምር እየከፈሉ የየራሳቸውን ሃይማኖት እንደያዙ በሰላም መኖር ፡

፫ኛ) ወይም ከሁለቱ አማራጮች ሁሉንም አንቀበልም ብሎ በሰይፍ መቀጣት ናቸው።

ዐረቦች ግብጽን እንደያዙ ኮፕቶች ፡ መለካውያንና አይሁድ የእስልምናን እምነት ለመቀበል ሳይገደዱ የየራሳቸውን እምነት በሰላም እየፈጸሙ እንዲኖሩ ተፈቀደላቸው ነገር ግን ክርስቲያኖችና አይሁዶች በጦር ሠራዊት ውስጥ ገብተው እንዲዋጉ ስለማይፈቀድላቸው ፤ ዘምተው በመዋጋት ፈንታ እስላሞች ከሚከፍሉት ሕጋዊና መደበኛ ግብር በተጨማሪ በግዴታ እንዲከፍሉ የተጣላባቸው የነፍስ ወከፍ ግብር እየተቀነሰ ሄደ በማለት አልፎ አልፎ በተለይም በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች እስልምናን እንዳይቀበሉ ያገዱበት ጊዜ ነበር።

የቤዛንታይን ገዥዎች የፖለቲካና የሃይማኖት ነጻነት ተነፍገው የነበሩት ኮፕቶች ምንም እንኳን ዘላቂነት ባይኖረውም ለመጀመሪያ ጊዜ የእምነት ነጻነት አገኙ ። ገዥዎቻቸውና ጨቋኞቻቸው ከነበሩት ከመለካውያን ጋርም በዐረቦች ዘንድ እኩል ይታዩ ጀመር ። ከመለካውያን ከነ አቡነ ሲሩስ ጭፍጨፋ በመሸሽ በስደት ገዳም ይኖር የነበረውም የኮፕቶች ፓትርያርክ ቀዳማዊ ብንያም ወደ እስክንድርያ እንዲመለስ ስለተፈቀደላት ወዲያው ተመልሶ የፓትርያርክነት ተግባሩን በሰላም ቀጠለ ።

የቅብጥ ቋንቋም በኮፕቶች ዘንድ በግሪክኛ ምትክ የመግባቢያ ቋንቋ ሆኖ ይሠራበት ጀምር ነገር ግን በአብደላ ኢብን እብደል ማሊክ ትእዛዝ ፯፻፭ ዓ/ም የመንግሥቱ ቋንቋ ዐረብኛ ብቻ እንዲሆን በታወጀው መሠረት ኮፕቶች በዐረብኛ መናገርና የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን ማከናወን ግዴታ ስለሆነባቸው የቅብጥ ቋንቋ ቀስ በቀስ እየተዳከመ ስለሄደ የኮፕቶች የመግባቢያ ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ ለሥርዓተ ቅዳሴ መፈጸሚያ ብቻ ሆኖ ቀረ ። የእስክንድሪያ ቤተ ክርስቲያን እስከዛሬ ድረስ ለሥርዓተ ቅዳሴዋ የምትጠቀምበት ይኸው ቅብጥ የተባለው ቋንቋ ነው ።

ኮፕቶች በጨካኙና በአእምሮ ቢሱ በከሊፋ አልሐኪም (፱፻፺፮ — ፩ሺ፳፩) ከፍ ያለና የሚዘገንን





www.ethiopianorthodox.org

ሥቃይ ደርሶባቸዋል ። እንዲሁም ከከሊፋ አልሐኪም በፊትና በኋላ በተነሱ ከሊፋዎች ዘመን መንግሥትም ክርስቲያኖች የተለየ ልብስ እንዲለብሱና ፈረስ እንዳይጋልቡ አልፎ አልፎ ይከለከሉ ነበር ።

ሆኖም ከአልሐኪም በኋላ በወራሹ በአል ዛሔር (፩ሺ፳፩ — ፩ሺ፴፯) ዘመነመንግሥት ለክርስቲያኖች የሃይማኖት ነጻነት እንደገና ሰጣቸው የፈራረሱት አብያተ ክርስቲያናትም ታደሱ ። ኢየሩሳሌም በጌታ መቃብር ላይ ተሠርቶ የነበረውና በአል ሐኪም ትእዛዝ የፈረሰው ቤተ ክርስቲያን በአል ዛሔር ትእዛዝ እንደገና ተሠራ ። በዚሁ ዘመን የእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ አዲስ ወደ ተመረጠችዋ መናገሻ ከተማ ወደ ካይሮ ተዛወረ ። ይህ የተደረገው በክርስቶዱሎስ የፓትርያርክነት ዘመን ነበር ። (፩ሺህ፵፯ ፩ሺ፸፯) ። እንዲሁም ታግደው የነበሩት የኮፕት ዐበይት በዓላት እንዲከበሩ ተፈቀደ ።

እላይ እንደተመለከትነው አብዛኛውን ጊዜ ያ ሁሉ መከራና ሥቃይ ቢፈጸምባቸውም ኮፕቶች እንደ ሊብያ ፣ ሰሜን አፍሪካና ኑብያ ክርስቲያኖች ሳይደመሰሱ (ሳይጠፉ) ፣ የምእመናኖቻቸው ቁጥር እየመነመነ ቢሄድም ቅሉ እስከዛሬ ድረስ ቀጥተኛው የተዋሕዶ እምነታችንን ጠብቀው ይኖራሉ ።

መ/ሉሌ መልአኩ

# ቂርቆስና ኢየሉጣ

የቅዱስ ቂርቆስ እናት ቅድስት ኢየሉጣ በሮም ግዛት ውስጥ በምትገኝ እንጌቤን በምትባል ቦታ የምትኖር ክርስቲያናዊት ሴት እንደነበረች ገድሉ ይናገራል ። ዘመኑም ዘመነ ሰማዕታት በመባል የታወቀ አምልኮተ ጣዖት የተስፋፋበት ፣ ክርስቲያኖች የሚሰቃዩበትና የሚሰደዱበት ዘመን ነበር ። በዘመኑ የነበረው አርያኖስ የተባለው አገረ ገዥ ቅዱስ ቂርቆስ ገና የሦስት ዓመት ሕፃን እንዳለ ከእናቱ ጋር ወደ አደባባይ አስጠርቶ ፈጣሪያቸውን እንዲክዱ ፣ ለጣዖት እንዲሰግዱ አዘዛቸው ።

ሕፃኑ ቂርቆስም የንጉሡን ትእዛዝ ሳይፈራ ፣ ስለ እምነቱም ሳያፍርና ሳይጠራጠር ሰማይና ምድርን ፍጥረታትንም ሁሉ በፈጠረ አምላክ እንጂ በሰው እጅ ለተሠሩ ጣዖታትን ማምለክ ሆነ ለነሱ መስገድ አይገባም በማለት ስለክርስቶስ በሰፊው መሰከረ አነጋገሩንም የአዳመጡ ሁሉ ከማድነቅና ከመገረም አልፈው ፈሩ ።



ቅ ገብርኤል ፫ቱ ደቂቅን ከእሳት ነበልባልእንዳዳነ ።

አገረ ገዥው መኰንንም የሕፃኑ ንግግር ሰውን የሚስብና የሚያሳምን መሆኑን ካየ በኋላ ጣዖታቱ ዋጋ ቢሶች ከምንም የማያድኑ መሆናቸውን ፣ እሱም ከክብሩ የተዋረደ መሆኑን በአደባባይ ስለ ተገለጠበት ሕፃኑ ቂርቆስና እናቱ በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ አዘዘ ።

ከዚህም በኋላ ትልቅ የብረት ጋን አምጥተው በውስጡ ነዳጅ በመሙላት እሳት ሲለኩሱበት የእሳቱ ወላፈን ድምፅ እንደክረምት ነጐድጓድ ሲያስተጋባ በሰማችና ነበልባሉን ባየች ጊዜ ቅድስት ኢየሉጣ ደነገጠች ከእራሷ ይልቅ ገና እድገ ያልጠገበችው የሦስት ዓመት ሕፃን በእሳቱ ውስጥ መጣል ስለዘገነናት ፈራች።

ሕፃኑ ግን "ጥብእኬ እም ወእትናፍቂ" እናቱ ሆይ ጨክኝ አትፍሪ አትጠራጠሪ ተጋድሎአችን በዚሁ መፈጸሙ ስለሆነ ዛሬ ፈጣሪያችንን ክደን ለዘለዓለሙ ስንቃጠል ከምንኖር ዛሬ አንድ ጊዜ ብንሞት በመንግሥተ ሰማያት ለዘለዓለሙ ሕያው ሆነን እንኖራለን ሥጋችንን እንጂ ነፍሳችንን አያቃጥሏትም በማለት አጽናናት" ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ ፣ ማቴ.፲ ፣ ፳፰ ከዚህ በኋላ የማይክዱ መሆናቸውን ስላረጋገጡ ወደ ነደደው እሳት ጨመሩዋቸው በዚህም ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ደርሶ እሳቱን ቢባርከው ሊያቃጥላቸው አልቻለም እንደውሃ ቀዝቅዞላቸዋል ሥጋቸውን ቀርቶ ልብሳቸውን እንኳ አልነካውም ። ይህንንም ከተመለከቱት ሕዝብ ብዙዎች በእግዚአብሔር አምነዋል ።

ከእመኑትም ውስጥ የሕፃኑ ቂርቆስንና እየሉጣን አርአያነት በመከተል በእምነታቸው ጸንተው ስለ ክርስቶስ መስክረው በሰማዕትነት ሕይወታቸውን በማሰለፍ የጽድቅ አክሊልን የተቀዳጁ ብዙዎች ናቸው ።

ሠለስቱ ደቂቅ ንጉሡ ናቡከደናፆር ላቆመው (የወርቅ) ምስል እንሰግድም በማለታቸው ወደ እቶን እሳት እንዲጣሉ አዞ ነበር ። ነገር ግን በእምነታቸው ጽንአት ፣ በቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት እሳቱ ምንም ሳይነካቸው ድነዋል። ንጉሡም ይህንን ድንቅ ተአምር አይቶ "ተአምራቱ እንዴት ታላቅ ነው እንዴትስ ጽኑ ነው? መንግሥቱም የዘለዓለም መንግሥት ነው ግዛቱም ለልጅ ልጅ ነው" ሲል በማድነቅ አመስግኖ አምኖአል ዳን ፬ ፫ ። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ ያለእንደ አምላክ በስተቀር ፣ ጣዖት የሚያመልክ ቢኖር እንዲቀጣ ትእዛዝ አስተላልፎ አል። ዳን ፫ ፣ ፳፰፡፳፱ ።

በሥጋዊ ጥቅምና በአንዳንድ ዘመን አመጣሽ ነገሮች ተታለን ከፈጣሪያችን እንዳንርቅ ምንም መከራና ችግር ቢደርስብን እንኳ እምነታችን ጽኑዕ መሆን እንደሚገባው የነዚህ ቅዱሳን ታሪክ ያስተምረናል "መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ ነገር ግን ባለጠጋ ነህ እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ" ራዕ.፪.፱.፩ ፣

የአምላክ ስጦታ ሴት ወንድ ትንሽ ትልቅ ሳይል በአመኑትና በወደዱት ሁሉ ላይ እያደረ ያናግራል ፣ "እምአፈ ደቂቅ መሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ ተብሎ ቀደም ሲል በ' ቢዩ ዳዊት እንደተነገረ በዚህ በሦስት ዓመት ልጅ ላይ መንፈስ ቅዱስ አድሮ የእግዚአብሔር ክብር በእርሱ እንዲገለጥና እንዲመሰገን አደረገ ።

ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ጥራቱ እንደሚታወቅ ሁሉ ሰማዕታትም የቀድሞ ነቢያትና ሐዋርያት እንደሆኑት ሁሉ በእሳትና በስለት ተፈትነው ፣ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ ፣ በሰይፍ ተቆርጠው ሞቱ" ሁሉን እያጡ መከራ እየተቀበሉ ፣ እየተጨነቁ ፣ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ.ዕብ ፲፩–፴፯ በዚህ ዓይነት የወንጌል ምስክሮች በመሆን የመጨረሻውን እስበ ተጋድሎ የክብር አክሊል ተቀዳጅተዋል ።

አማኞችም እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆናቸው የሚረጋገጠው በሥጋዊ ጥቅም የማይደለሉ በወገንና በገንዘብ ተለውጠው በሐሰት የማይመሰክሩ በዕውነት የሚፈርዱ ፣ የሀገርና የወገን ፍቅር ያላቸው ወንድምና እኅቶቻቸውን እንደራሳቸው የሚወዱ በሕገ እግዚአብሔር የጸኑና ማናቸውም ፈተና በደረሰባቸው ጊዜ የማይለወጡ ሲሆኑ ነው ።

በዚህ ዓይነት ተጋድሎ ቅዱሳን አባቶቻችን ያቆዩንን ሃይማኖት በክብር ተቀብለን መጠበቅና በተሰጣቸውም ቃል ኪዳን መሠረት ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንድናገኝ መታሰቢያቸውን እያደረግን የነሱን ፈለግ እንድንከተል ከሁላችን ይጠበቅብናል ።

መንክር ዋሴ.





www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በክርስትና ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች በትድሚያ ሊያለሙ የሚገባቸው ምን እንደሆነ የሃይማኖት ሊቃውንት ምስክርነታቸውን ሲሰጡ "የሰዎች ሕይወት በቃለ እግዚአብሔር ያሸበረቀ ከሆነ ተከታዮቹ ሁሉ ከመነገራቸው አስቀድመው የሚመለከታቸውን ሥራ መክረና አስተማሪ ሳይፈልጉ ሊሠሩ ይችላሉ በትምህርት ከልታነፁ ግን ሁልጊዜ ምክርንና መመሪያን በመጠባበቅ ይኖራሉ" በማለት ይናገራሉ ።

ይህ ትምህርታዊ አነጋገር ሰዎች የተፈጥሮ ዕውቀታቸውን በትምህርት ክአዳበሩ የሰሙትንና ያዩትን ፈጥኖ የመቅረጽና የመሥራት ፍላጎት ይኖራቸዋል ።

በዓለም ውስጥ መንፈሳዊ ልማት የማይታይባቸውና የእግዚአብሔር ቃልም ያልደረሳቸው ሰዎች እንዳሉ ግልጽ መሆኑ እየታወቀ በአስተማሪ እጥረት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ጠምቷቸው ሕይወታቸው በቃሉ ሳይለማ እንደሚኖሩ ከማንም የተሠወረ አይደለም ።

በሀገራችን እንኳን በአንዳንድ አከባቢ ልማት ለማልማት ይቅርና በየጠረፉ ያሉት ወገኖቻችን አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽሙባቸው አብያተ ክርስቲያናት ባለመኖራቸው ምን ያህል ጥያቄ እንደሚቀርብ ለሁሉም ግልጽ ነው ።

የልማት ተግባር በአንድ ዓይነት መንገድ የሚከናወን ሳይሆን በተለያዩ መንገዶች የሚከናወን መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል ፤ ያልተማሩትን አስተምሮና አሰልጥኖ ለማስተማር እንዲበቁ ማድረግ ለቤተ ክርስቲያናችን የመጀመሪያውም የልማት ክፍል መሆኑን መረዳት አለብን ።

የፈራረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ ያልታነፁ እንዲታነፁ ጉልበትን ገንዘብንና ዕውቀትን ማስተባበር ሌላው የልማት ተግባር እንደሆነ እሙን ነው ። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ልዩ ልዩ የሆኑ የልማት ተግባሮችን እያቋቋሙ ካህናቱ እየጸለዩ ፤ እየቀደሱና ማኅሌት እየቆሙ ትርፍ ጊዜ ሲኖራቸው እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመንበታል ።

በዚህ "ልማት በቤተ ክርስቲያን" በሚለው ትምህርታዊ ዓምድ የሚቀርቡ ጽሑፎች ካህናት በትርፍ ጊዜያቸው ደክመን ሰለቸን ሳይሉ ራሳቸውን ረድተው ለሌሎች መልካም ምሳሌ ሆነው በመገኘት የልማት ተግባር ጀምረው የሚሠሩት እንዲበረቱና እንዲጠናከሩ ያልጀመሩት በመልካም ምሳሌነታቸው ተጠቅመው ተከታዮች እንዲሆኑ ለማድረግ ትምህርት ለመስጠት ነው ። በዛሬው ጽሑፋችን የምናቀርበው በአርሲ ሀገረ ስብከት በአሉት አውራጃዎችና በርእሰ ከተማው በሚገኙት የልማት ተቋሞች የሚካሄዱትን የልማት ሥራዎች በማስተዋወቅ አንባብያን እንዲረዱት ለማድረግ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን ።

በአርሲ ሀገረ ስብከት ከግንቦት ፳፫ እስከ ፳፰ በቆየንበት ወቅት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር በመሆን ልዩ ልዩ የልማት ቦታዎችን እንድንጐበኝ መልካም ፈቃዳቸው በመሆኑ የተለያዩ የልማት ተቋሞችን ተመልክተናል ።

በሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና በእየአውራጃዎቹ ሊቃነ ካህናት በቀረበው ሪፖርት እንደሰማነው በብዙ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የባሕር ዛፍና የልዩ ልዩ ዛፎች ተክላ ተካሒዶ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዛፎች እንደጸደቁ ተገልጿል ።

በተለይ በርእሰ ከተማው የግብርና ሚኒስቴርና የቀይ መስቀል ተከፋፍለው ችግኝ በሚያፈሉበት ቦታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ እንዲኖራት በማድረግ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ያደረጉት ጥረት በቀላሉ የማይገመትና የማይታይ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን በቃል ብቻ ማስተማር ሳይሆን በልማት ያላትን ተሳትፎ የሚያስረዳ ነው። በተለይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ "ደብር ቅዱስ" ተብሎ ለተሰየመው ቦታ ከሁለት ኪሎ ሜትር በላይ ርቀት ያለውን የመኪና መንገድ በማሠራት ለጐብኚዎች አመች ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ ለወደፊቱ ለሚሠራው የዕጓለ ማውታ አዳሪ ቤት ዕቅድ ለማዘጋጀት ለሚጓጓዙት ቁሳቁሶች ያለ እንዳች መሰናክል ከቦታው እንዲደርሱ ለማድረግ እንደሚያስችል ግልጽ ነው ።

የዚህ የተፈጥሮ አቀማመጡና በአካባቢው ያሉት ዛፎች ዓይንን የሚማርኩ ሕሊናን የሚሰበስቡ በመሆናቸው አንድ ጊዜ ከቦታው ከደረሱ ለቆ ለመውጣት ቅሬታን ያሳድራል።



## የሴቶች ዓምድ

# ድንግል ማርያም በኤልሳቤጥ ቤት

ድንግል ማርያም ጐጆ ነው ፤ እልፍኝ ነው ፤ አዳራሽ ነው ፤ ብላ አትመርጥም ቅድስት ድንግል ማርያም ደሀ ነው ፤ ባለጠጋ ነው ፤ ድሃ ናት፤ ባላጠጋ ናት ፤ ብላም ሁሉን በትክክል ከማየት በቀር ማንንም ከማን አትለይም ። ያጣውንም የነጣውንም ሁሉ በየችግሩ እየተገኘች ትረዳለች ቤቱንም በምህረት በሰላም ትጐበኛለች በተለይም የምግባር ቅድስና ፤ የልብ ንፅህና ፤ የተስተካከለ ሕይወት ያለውን እንደምትጐበኝ በኤልሳቤጥ ችግር መፍትሔ ማግኘት ታውቋል ።

---

ሀገረ ስብከቱ የተፈጥሮ አቀማመጡና ዛፎቹ በቂ ናቸው ሳይል በአካባቢው ብዛት ያላቸው የባሕር ዛፎች ቀደም ብሎ በመትከል እንክብካቤ ያደረገ ስለሆነ ለወደፊት ለሚሠሩት ቤቶች ራሱን እንደሚችል የማይተበል ሐቅ ነው ።

ስለአርሲ ሀገረ ስብከት የልማት እንቅስቃሴ አንድ በአንድ በዝርዝር ለማቅረብ ብዙ ጥናትና ጊዜ ስለሚያስፈልግ ሁሉንም በዚህ ጽሑፍ አቀረብን ማለት ሳይሆን "ያየነውን እንናገራለን የሰማነውን እንመሰክራለን" የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር በመከተል ብቻ ለማስገንዘብ መሆኑን አንባብያን እንዲረዱልን እንፈልጋለን ።

ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ
ወንድም

የኤልሳቤጥ ችግር ምን ነበር የተባለ እንደሆነ እርሷም በሁለት ነገር ተጨንቃ ነበር ፤

፩ኛ) ባለቤቷ ለአገልግሎት ቤተ መቅደስ በነበረበት ጊዜ የመልአኩን ብሥራት ባለማመኑ ምክንያት መናገር ሳይችል ዲዳ ሆኖ ወደ ቤቱ በመመለሱ ምን አግኝቶት ይሆን እያለች ታስብ ነበር ።

፪ኛ) በሴቶች የሚሆነው ደንብ ሙቀትና ልምላሜ ከተለያት በኋላ በመፅነሷ እፍረት ስለተሰማት ላለመታየት እራስዋን ከሰዎች ዘንድ ለአምስት ወራት ያህል ሰውራ እንዴት ሊሆን ይችላል? እያለች ታሰላስልና ትጨነቅ ነበር። ጭንቀቷ ይህ ብቻ አልነበረም ። በሩቅም ሆነ በቅርብ ያሉት ዘመዶቿና ወዳጆቿ ጐረቤቶቿም ሆኑ የሚያውቋት ሁሉ ሸሽተዋት የሚያነጋግራት አጥታ ብቸኛ በመሆኗ ግራ ገብቷት ስለነበር ድንግል ማርያም ልታፅናናት ችግሯን ልታቃልልላትና ልትጐበኛት ወደ ኤልሳቤጥ ቤት ሄደች።

ስለዚህም ወንጌላዊው ሉቃስ እንደሚለው "ድንግል ማርያም ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች ወደዘካርያስም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምፅ ጮኽ ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት ከሴቶችም መካከል የተባረክሽ ነሽ" ስትል ንፅሕናዋን ቅድስናዋን ለአመነባት ሁሉ ርኅርኅት መሆኗዋን መሰከረች ሉቃ ፩—፴፱—፵፮

ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ስላደረባትና ድንግል ማርያም በምህረት በቸርነት ስለጐበኘቻት አርጅቶ የነበረው ሕይወቷ ታደሰላት ችግሯም ተቃለለላት ስለእንዲህ ያለውም አዲስ ሕይወት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ፪ኛ ቆሮ ም፭ቁ ፲፯ ሲጽፍ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌ ነገር አልፏል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል" ብሎ ተናግሯል ።

እንዳለውም ኤልሳቤጥ በድንግል ማርያም ጉብኝት በልጇ በክርስቶስ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ፍጥረት በመሆኗ አዲስ ኃይል በማግኘቷ መንፈስንም በመላበሷ ብቸኝነቷም ችግሯም ሊወገድላት ችሏል ።

እንግዲህ ቅድስት ድንግል ማርያም የምትጐበኘው ኤልሳቤጥን ብቻ አይደለም ዛሬም በዘመናችን የፍልሰቷን በዓል የሚያከብሩትን ፤ የፍልሰቷን ጾም የሚጾሙትን ፤ በጠቅላላ በከተማም ሆነ በገጠር የሚኖሩትን ሁሉ ጐጆ ፤ እልፍኝ ፤ አዳራሽ ሳትመርጥ በልጇ የሚያምኑትን በእርሷ የሚማፀኑትን ቤታቸው ሰላም እንዲሆን ሕይወታቸው እንዲጠበቅ ሀብታቸው ንብረታቸው እንዲበረክት በምህረት በቸርነት ትጐበኛቸዋለች ።

ይህ ከሆነ ከነሐሴ ፩ ፲፮ ባሉት ቀናት ማንኛውም ክርስቲያን ሴት ወንድ ሽማግሌ ወጣት ታዳጊ ሕፃናት የሆኑ ሁሉ ጧት ጧት በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ የውዳሴዋን ፤ የቅዳሴዋን ትርጉም እንዲያዳምጡ ይፈለግባቸዋል ። በእኩለ ቀንም በስድስት ሰዓት



www.ethiopianorthodox.org

የሚሰበከውን ቅዱስ ቃሉን መስማትና የቅዳሴው የጸሎቱ ተካፋይ ሊሆኑ ይገባቸዋል ። የቅዳሴ ጠበል መጠጣት ብቻ ሳይሆን ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ያለውን ቃል አክብሮ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ያስፈልጋል ።

እናቶችም የሆኑ ሁሉ ልጆቻቸው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት እንዲለምዱና የጾምን ጠቃሚነት እንዲያውቁ ንጽህናቸውን ጠብቀው ትምህርቱን እንዲሰሙ የእመቤታችን ድንግል ማርያምን አማላጅነትና የሰው ልጆች ፍቅር እንዳላት እንዲረዱ ለእነርሱም መልካም ሕይወት እንደምትሰጣቸውና በጥበብ ፣ በሞገስ ፣ በመንፈስ እንድታሳድጋቸው ከልጅ እንደምታማልዳቸው ከመግለፅ ባሻገር ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው መጥተው እንዲያስተድሱና ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ ፣ በድንግል ማርያም ስም እንዲዘምሩ ማድረግ ከእናቶች ይጠበቃል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ሥነ ሥርዓት ማስከበርና ማስተማር ስላለባት አስተናጋጆች የሆኑት ዲያቆናት ትምህርት ሊሰሙ፣ ሊያስቀድሱ የሚመጡትን እንግዶች ሁሉ ማንንም ከማን ሳይለዩ ሁሉንም በእኩልነት ተቀብለው በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ማስተናገድ ይኖርባቸዋል ። ሕፃናት እንዳይንጫጩ ከወዲያ ወዲህ እንዳይሯሯጡ ሴቶችን በሴት ወንዶችን በወንድ በየቦታቸው ቆመው እንዲያስቀድሱ ሥነ ሥርዓት ማስያዝ በመቆጣት ፣ በመገላመጥ ፣ በመምታት ሳይሆን በማስተማር በመመከር ሥነ ሥርዓቱን ማስፈፀም አክብሮ ማስከበር ከዲያቆናት የሚጠበቅ ታላቅ ዝግጅት ነው ።

ሥርዓተ ቅዳሴውም ተፈጽሞ ቅዳሴ ጠበል በሚታደልበት ጊዜ በታዳዩ መካከል ጩኸትና ፍጅት እንዳይኖር በዝምድናው በውቂያ ሚሆኑ ቀርቶ በርጋታና በመንፈሳዊ ዲሲፒሊን በተራ ለሁሉም በእኩልነት ማደል ከዲያቆናት ይፈለጋል ።

በዚህ አኳኋን ከተፈፀመ የፍልሰተዋ ጾም የበረከት ፣ የሰላም ፣ የአንድነት ፣ የፍቅር ጾም ስለሚሆን እመቤታችን ድንግል ማርያም ደስ ይላታል ። ሁሉንም በረድኤት ትጐበኛቸዋለች ። "እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓል። ስሙም ቅዱስ ነው" ስትል የተናገረችው ቃል በተግባር ይተረጐማል ሉቃ ፩ ፡ ፵፱—፶ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሁሉ እያከበርን የፍልሰተዋን ጾም የጾምን እንደሆነ ዋጋችን ከፍ ያለ ሕይወታችን የተደላደለ ይሆናል ጾም የዘላለም አክሊል የሚያጐናጽፍ ኃጢአትን የሚያስተሰርይ ዋጋን የሚያሰጥ ለሀገር ሰላምን የሚያመጣ ፣ በረከትን የሚያድል ነውና በአፍ ብቻ ሳይሆን በልብም መጾም ያስፈልጋል ።

ስለዚህ ድንግል ማርያም እንድትጐበኘንና መንፈስ ቅዱስ እንዲያድርብን የፍልሰተዋን ጾም በምንጾምበት ጊዜ እንደኤልሳቤጥ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው እያልን በሰፊው እንመስክር።

ወ/ት መዓዛ አስማማው

# የደብረ ጽጌ…

(ከገጽ ፳፬ የዞረ)

ጻድቁ አቡነ እንድርያስ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ትእዛዝ ወደ አሥመራ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እየተመላለሱ ይቀድሱ ነበር ከዚህም በኋላ ጻድቁ አቡነ እንድርያስ ከሐበላ ተነሥተው ዓዲ ነህባይ ማደምጭቃ ወደተባለው ቦታ ሄደው ሱባኤ ገቡ ።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ይህ ቦታ ክፍልህ አይደለምና ወደ ጼዳርዋ ሂድ ሲላቸው ወደዚሁ ቦታ ገብተው በጺጻርዋ ጋራ ሥር ከዋሻ ገብተው ሲኖሩ ጠበል ፈልቆላቸዋል ።

ጻድቁ አቡነ እንድርያስ የአንድነትን ማኅበር አቋቁመው ገዳሙንም ደብረ ጽጌ ብለው ሰይመውገዳሙንም በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት አስገድመውታል ።

በዚህ መንፈሳዊ ሥራ ከኖሩ በኋላ ስማቸውን የጠራ እሳቸው ከገቡበት ውሳጤ መንጠላዕት እንደሚገባ ከፈጣሪያቸው ቃል ኪዳን ተቀብለው የካቲት አንድ ቀን ስላረፉ አርቶዳክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የካቲት ፩ ቀን መታሰቢያቸውን ታደርግላቸዋለች ።

ይህ ደብረ ጽጌ የተሰኘው ገዳም ዓጽማቸው ካረፈበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዋሻቸውና ሱባዔ ይገቡበት ከነበረው በዓት የፈለቀው ጠበል ማንኛውንም በሽታ ሲፈውስ ይኖራል ።

ዋሻውም የሚገኘው ከቤተ ክርስቲያኑ ፵፰ ሜትር ወደ ውስጥ አልፎ ነው ። ቤተ ክርስቲያኑ በስዕሉ እንደተመለከተው በጋራው ሥር ነው የሚገኘው ።

መ/ክነፈርግብ ማርቆስ



# ዜና ሊቃውንት

እስካሁን ድረስ በዚህ አምድ የሚቀርቡት በጉባኤ የዋሉ ምሥጢር ያደላደሉ በእድሜ የገፉ የዜማ የቅኔና የመጻሕፍት መምህራን ሲሆኑ ዛሬ ደግሞ የምናቀርባቸው በአቋቋም መምህርነት ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ላይ የሚገኙትን መሪጌታ ዘለዓለም ያየህን ይሆናል።

መሪጌታ ዘለዓለም ያየህ በምዕራብ ጐጃም አስተዳደር ክልል በባሕር ዳር አውራጃ ከአዴት ከተማ በ፫ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው በጥንታዊቷ ገዳም ጌቴ ሴማኒ ማርያም መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ከአባታቸው ከአቶ ያየህ እንግዳ እና ከእናታቸው ከወ ሮ የሩቅነሽ ያዩ ተወለዱ እድሜአቸው ለትምህርት እንደደረሰም በተወለዱባት በጌቴ ሴማኒ ማርያም አባ አላባ ይባሉ ከነበሩት መምህር ከፊደል ቆጠራ እስከ ንባብ ድረስ ተምረው ከዚያም ወደ ደብረ መድኃኒት አዴት መድኃኔ ዓለም ገዳም በመሐድ ጐንደሬው ካሳ እየተባሉ ይጠሩ ከነበሩት ሊቅ ከአፈ መምህር ካሳ ትርፌ ከንባብ እስከ ዳዊትና ቃል ትምህርት በመማር ላይ እንዳሉ እኒሁ ሊቅ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው አሁንም በዚሁ በደብረ መድኃኒት አዴት መድኃኔ ዓለም በሕይወተ ሥጋ በማስተማር ላይ ከሚገኙት ከመሪጌታ ለይኩን ደስታ የድጓ መምህር ትምህርታቸውን በመቀጠል ጾመ ድጓ እና ምዕርፍ አጠናቀው ከተማሩ በኋላ ወደ ጐንደር ክፍለ ሀገር በሙሐድ በቆላ ድባ ወረዳ ደብረ መንክራት አሽራ ማርያም ከመሪጌታ ዘለዓለም መንግሥቱ አቋቋም ለአምስት ዓመታት በሚገባ ተምረው አውቀዋል ። እንደገናም በአለፋ ጣቁሳ ወረዳ ለምና ማርያም ከነበሩት የቅኔ መምህር ከመምህር ቂርቆስ ቅኔ ከነአገባቡ ተም



መሪጌታ ዘለዓለም ያየህ ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር

ረው አውቀዋል ። ከዚያም ትምህርታቸውን በመቀጠል አምስት ዓመታት የደከሙበትን የአቋቋም ትምህርት ከግቡ ለማድረስና በዚሁ ሙያ ለመመረቅ ጎንደር ከተማ በምትገኘው በደብረ ኃይል በዓታ የአቋቋም ምስክር ከሆኑት ከመምህር ሄኖክ ወ/ሚካኤል ዘንድ ይኸንኑ ሙያ ከነይት በሃሉ በማደስ ከመመረቃቸውም በላይ እንዲያስተምሩ የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

መሪጌታ ዘለዓለም ያየህ ለመጀመሪያ ጊዜ በአቋቋም መምህርነት ጉባኤያቸውን የዘረጉት በጭልጋ አውራጃ ለዛ በአታ ከተባለችው ደብር ነበር በዚያ ለአንድ ዓመት ያህል ከአስተማሩ በኋላ ወደአለፋ ጣቁሳ በመሐድ ስሜ ሚካኤል ከተባለው ደብር የማስተማር ስራቸውን በመቀጠል ለአምስት ዓመታት ያህል አስተምረዋል ከዚያም ወደ ትውልድ ሀገራቸው ወደ ጎጃም በመመለስ በተወለዱባትና ከሕፃንነታቸው ጊዜ ጀምረው ፊደል በቆጠሩባት በጌቴ ሴማኒ ማርያም ገዳም የተለመደውን ጉባኤያቸውን በመዘርጋት የማስተማር ተግባራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ብዙ ሊቃውንቶችን አስተምረው አበርክተዋል ። መሪጌታ ዘለዓለም ያየህ ማስተማር ብቻ ሳይሆን በእድሜ የገፉ ማለትም ጐልማሳ ተማሪዎችን እንደ ወንድም ታናናሾችን ደግሞ ልጅ በመምክርና በማስተማር እውቀታቸውን ከመለገሳቸውም ሌላ በመልካም ሥነ ምግባር የታነጹና የተሞሉ አባት ለመሆናቸው በአሁኑ ጊዜ ጉባኤያቸው ደምቆና ሰፍቶ ለመገኘቱ የሊቁ ሕያው ምስክርነት ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በጐጃም ወነባ ቅ/ሚካኤል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን ለመመረቅና ለመባረክ በቦታው በተገኙ



www.ethiopianorthodox.org

በት ጊዜ የመሪጌታ ዘለዓለም ያየህ የተማሪዎቻቸው ብዛትና የራሳቸውም የሞያ ብቃት በቅዱስነታቸው ዘንድ ታይቶና ተገምግሞ ለመሪጌታ ዘለዓለም ያየህ ከቅዱስነታቸው የገንዘብ ስጦታ ተደርጎላቸዋል ።

እውቀትን ከሥነ ምግባር ጋር አስተባብረው የያዙት እኚህ ሊቅ ፋሺሽት ኢጣሊያ ከ፲፱፻፳፰ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ድረስ ሀገራችን ኢትዮጵያን በእብሪት በወረረበት ወቅት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠሉና መመዝበሩ የሚዘነጋ አይደለም ስለሆነም በዚያን ወቅት ከተቃጠሉትና ከተመዘበሩት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የጌቴ ሴማኒ ማርያም ገዳም በመሆን ትገኛለች ይች ገዳም በኢጣሊያ ወረራ ብርቅና ድንቅ የሆኑ የብራና ወጻሕፍቶች መስቀሎችና የተለያዩ አልባሳት ቤተ ክርስቲያኗ ስትቃጠል አብረው ተቃጥለዋል ወድመዋል ።

ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኗ እስካሁን ድረስ ሳትሰራ በመቆየቷ መሪጌታ ዘለዓለም ያየህ ሁኔታው እንገብግቧቸውና አስገድዷቸው።

ቤተ ክርስቲያኗን ለማሠራት ከሰበካው ሕዝበ ክርስቲያን ጋር በመወያየት የቤተ ክርስቲያኗ አሰሪ ኮሚቴ ሲቋቋም ራሳቸው የኮሚቴው ሊቀ መንበር እና የሥራው ኃላፊ በመሆን የቤተ ክርስቲያኗ ሥራ እንዲጀመር አድርገዋል። በመሆኑም የአጥቢያው ሕዝብ ወንዱ እንጨት በመቁረጥና በመፍለጥ ድንጋይ በማገዝና ጭቃ በማቡካት ከፍተኛ የስራ ድርሻ ያበረከቱ ሲሆን ሴቶች ደግሞ ከሩቅ ቦታ ውሃ በመቅዳትና ለሠራተኞች እህል ውሃ በማቀበል የሚያስደንቅ የሥራ ድርሻ አድርገዋል ።

አሁን ቤተ ክርስቲያኗ የቀለምና የመስተካከል ሁኔታ ቢጎድላትም ታቦቷ ወደ አዲሱ ሕንፃ እንድትገባ አድርገዋል ። መሪጌታ ዘለዓለም ያየህ ባሁኑ ጊዜ በማስተማር ቤተ ክርስቲያን በማገልገል በብሕትውና የሚኖሩ ታላቅ አባት ናቸው ።

ኢሳይያስ ደምለው

# ጠባይህን አሻሽለሃል?

ይህ አባባል በየመሥሪያ ቤቱ ፣ በየትምህርት ቤቱና በየፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚቀርብ ተግሳፅ ምክር ቢሆንም ጥቂቶቹ ሲጠቀሙበት ሆኖ የተገኘ አይመስልም ። ሙበት ሆኖ የተገኘ አይመስለም። ጠባይ እንደሸቀጥ እቃ የሚገዛ አይደለም እንደሸሚዝም በየቀኑ አይለወጥም እንደ እንጨት አይጠረብም ከዱር እንደተቆረጠ ሞፈር በእሳት ተለብልቦ አይታረቅም ጥሩ ጠባይ በሰው ሕይወት ውስጥ ሲያበራ የሚኖር የሕይወት መቅረዝ መሆኑን ሰዎች ሊያውቁት ይገባል ።

ሊቃውንት እንደሚሉት ጠባይ በአጠቃላይ መልኩ ሁለት ዓይነት ነው አንደኛው ጥሩ ጠባይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ክፉ ጠባይ ነው ። ክፉ ጠባይ ያዋርዳል ጥሩ ጠባይ ከፍ ከፍ ያደርጋል ። ሰውን የገዛ ጠባዩ እንደሚጥለው ጠላት እንኳን ሊጥለው አይችልም ።

ለምሳሌ የአስርቆቱን ይሁዳን ብንመለከት በመጀመሪያ ጊዜ ጥሩ ጠባይ ይዞ ወደ ክርስቶስ ቀረበ ክርስቶስም ስለመልካም ጠባዩ የገንዘብ ኃላፊ አድርጎ ሾሞት ነበር ። እንደገና ጠባዩን ለወጠና ታምኝነቱን ከማጉደሉም ሌላ ክርስቶስን በገንዘብ ለወጠው ። እንደገና ደግሞ ሸጦ ያገኘውን ሰላሳ ብር በጥቅም ላይ በማዋል ፈንታ ጠባዩ ተለዋዋጭ በመሆኑ አልፈልግም ብሎ ለሰጡት ሰዎች ለመመለስ ሄደ እነሱም እንቀበልህም ቢሉት በቤተ መቅደስ በትኖት ሄደና ታንቆ ሞተ ። ይህም የጠባይ መለዋወጥ አይጠቅምም ከታማኝነትም ያወጣል የመንፈስ ምስኪን ከማድረጉም ባሻገር የሥራም የታሪክም ደሀ ያደርጋል ።

ስለጠባይ ጴጥሮስን ብንመለከት ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥሩ ጠባይ ነበረው ይኸውም ክርስቶስ በአይሁድ እጅ እያዛለሁ እያለ በሚናገርበት ጊዜ እኔ አብሬህ እሞታለሁ ፣ እኔ አብሬህ መከራ እቀበላለሁ እያለ የፎከረው ጴጥሮስ ጠባዩን ለወጠና ዶሮ እስኪጮህ ሶስት ጊዜ በአደባባይ ካደው እንደገና ደግሞ ይህን የመሰለውን መጥፎ ጠባይ ለወጠና መራራ እንባ እያለቀሰ ንሰሐ በመግባቱ ተሰጥቶት የነበረው የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ በጥሩ ጠባይ እንደገና ሊመልሰው ችሏል ጠባይ ያዋርዳል ጠባይ ያስከብራል የሚባለው ከዚህ የተነሳ ነው ።

በመሆኑም ይሁዳ ጠባዩን አላሻሽልም በማለቱ በጠባዩ ሲዋረድ ጴጥሮስ ግን ጠባዩን አሻሽሎ በመገኘቱ ከበረ ። ከፍ ከፍ አለ ። የሐዋርያትም አለቃ ተብሎ ተሾመ ጠባይ ስሚንቶን ይመስላል የኸውም ስሚንቶ በአዲስነቱ አይለጠጥም በጥቅም ላይ ይውላል እየዋለ እያደረ ግን ነፋስ ሲገባው ይጠጥራል እንደቆየ መጠንም የዘላለም ቅርጹን ይዞ ይቆያል ።

የሰው ልጆችም ከእናታቸው ማህፀን ሲወለዱ ወደ ዓለም ንጹሕ ወረቀት ሆነው ይገባሉ ሲሞቱም ከዚህ ሕይወት የሚወስዱት ነገር በዚህ ዓለም ያፈሩትን ጠባይ ብቻ ነው ክፉ ጠባይ ያላቸው ደግሞ ያንኑ ክፉ ጠባይ ይዘው ይሄዳሉ ።

እግዚአብሔርም የጠባይ ገንቢ በመሆኑ በመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ ነፃነት ያለው አድርጎ ሰውን ፈጠረ ። ባገኘውም ነፃነት የወደደውን ለመሥራት መብት ስላለው መጥፎንም ሆነ ጥሩውን ጠባይ ሊፈጥረው የሚችለው እራሱ በራሱ ነው ለዚህም መረጃ የሚሆነን ሰይጣን መልአክ ሆኖ ተፈጥሮ ነበር ከጊዜ በኋላም ጠባዩን በመለወጡ ራሱ በራሱ በፈጠረው መጥፎ ጠባይ ጠባየ ብልሹ ሆኖ ተገኝና የመልካም ጠባይ ተቃራኒ መሆኑ ተገለጠ ።

አምላካችን እግዚአብሔር ጥሩ የሆነውን ሥራ ሁሉ ሚቀበልና ከመልካም ሥራ ጋራም ኅብረት ያለው አምላክ መሆኑን ስለሚረዳ ጠባየ ብልሹ የሆነው ሰይጣን እርሱ የሠራውን ሲንድና ዓላማውንም ሲያበላሽ ይኖራል ። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች ተፋቅረውና ተስማምተው እንዲኖሩ የምህረት እጁን ሲዘረጋ ሰይጣን ግን ይህ ሁኔታ ስለሚያስደስተው የሰው ሁሉ ጠባይ እንዲበላሽ እርስ በእርሱ ተጣልቶ እንዲለያዩ እንቅፋትና መሰናክል እያኖረ በሰዎች መካከል ጠብን ይዘራል ።

የሰይጣን ሥራ ይህ ብቻ አይደለም ። ተካሳሽም በመሆኑ ጠባየ መልካምና በሥራውም ጻድቅ የነበረውን ኢዮብ ለእግዚአብሔር ከሶ አቅርቦ ታላቅ በሽታ እንዲወድቅበትና ሀብቱንም ንብረቱንም ልጆቹንም እንዲያጣ አድርጎታል ኢዮብ ፩—፲፪—፳፪ ኢዮብ ግን ይህ ሁሉ መከራ ቢደርስበትም እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን ከማለት በቀር ጥሩ ጠባዩ አልተለወጠም ጠባዩ ባለመለወጡም እጥፍ ንብረት አግኝቷል ይህም ለክርስቲያኖች መልካም ትምህርት ሊሆን ይችላል ።

በዚህ ዓለም በሰው ልጅ ኑሮ በኩል ብንመለከት አንዱ ሌላውን የሚከስበት ምክንያት ምንድነው ? የተባለ እንደሆነ በጠባይ ጉድለት ሆኖ እናገኘዋለን በመሆኑም በተቻለው መጠን ሰውን በማጉደፍ ጠባዩን ክፉ ያደርጋል ምናልባት አንዳንድ እሱን የመሰሉ ሰዎች ሐሳቡን ይቀበሉት ይሆናል። አዋቂዎች ግን እራሱ ጠባየ ብልሹ መሆኑን ስለሚያውቁት መጀመሪያ ይመክሩታል ምክራቸውን አልቀበል ሲል ደግሞ መከራ ይምከረው ብለው ይተውታል ። ምንም እንኳን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ሙሉ ነፃነት ቢሰጠውም ጠባዩን እየለዋወጠ እራሱ ታውኮ ሌላውንም ሊያውክ አይገባውም ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር ምሳሌና መልክ በመሆኑ በሥራው በጠባዩም ፈጣሪውን መምሰል ለሌሎቹ ጥሩ አርአያ ሆኖ ሊታይ ያስፈልገዋል ። ዝቅተኞቹ እንኳን ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት በጠባያቸው ዝንባሌ ይመራሉ ይህ ስሜት አብሯቸው የተወለደ ነው ጥቂት በጥቂት እያሉ የሚማሩት ትምህርት አይደለም አብሯቸውም የሚሄድ አይሆንም እነርሱ ሕይወታቸውን በሚመሩቸው በተወሰኑት የተፈጥሮ ሕጎች ይመራሉ። በሰው ረገድ ግን ይህ አይደለም እንዳደገ መጠን መማር ይገባል ሲያድግም ሊመርጥ ይችላል አእምሮ ሕሊናና የፈቃድ ኃይል የተወሰነ የጠባይዝንባሌ ይሰጠዋል ።

በእነዚህ አስገራሚ ተግባሮች ሰው የራሱን ምርጫዎች ያደርግ ዘንድ ተፈቅዶለታል ። ግን እያንዳንዱ ምርጫ የሕይወቱን አቅጣጫ ለዘለዓለም የሚሆነውን የጠባዩን መደርጀት ያመለክታል ። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ሙሉ የሆነ የነፃነት ምርጫ ይሰጠናል የእስራኤል የጠባይን መለዋወጥ በየጊዜው የተመለከተው ኢያሱ እግዚአብሔርን ማምለክ ቢከፋችሁ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን ብሏል ኢያሱ ፳፬ ፣ ፲፭

ወደአለንበት ዘመን መለስ ያልን እንደሆነ አንዳንድ ሰዎች ጠባያቸውን ያሻሽላሉ ብለን ብንገምት እየባሰባቸው ሲሄዱ በየቀኑ የምናየው አርእስተ ጉዳይ ነው ይኸውም አሠሪን ከሠራተኛ ሠራተኛን ከአሠሪ አባትን ከልጅ ልጅን ከአባት ፣ ባልን ከሚስት ሚስትን ከባል ጎረቤትን ከጎረቤት ፣ ጓደኛን ከጓደኛ ሲያለያዩ ድል እንዳደረጉ ይቆጥሩታል እንዲህ ያሉትም ሰዎች እየበረከቱ በመሄድ ላይ ይገኛሉ ። ቢሰሙን ጠባያቸውን እንዲለውጡ ኃላፊነት ያለብን ሰዎች ሁሉ በአካባቢያችን ያሉትን ፣ በምክራችን በትምህርታችን ልንለውጣቸውና ጠባያቸውን እንዲያሻሽሉ ልናደርጋቸው ይገባናል ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# "ሞቶ ሙስ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ" ጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው

ጻድቅ የሚለው ቃል በምድራዊና በሰማያዊ መንግሥት ሕግ የሚመራ እውነተኛ ፡ ትክክለኛና ታማኝ ማለት ነው ፡ ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ሕግ ሲመሩና ሲኖሩ ጻድቃን ይባላሉ ፡ ይኸውም ከኅብረተሰቡ መካከል ወጥተው የዚህን ዓለም ጥቅምና ረብ ንቀው እምነታቸውን አጽንተው በንጽሕናና በቅድስና ራሳቸውን ለይተው ፡ በበጎ ተከተው በምግባር ፡ በሃይማኖት አሸብርቀው ሲኖሩ ጻድቃን የሚል ስም ይሰጣቸዋል ።

ጻድቅ ማለት ባጭሩ እውነተኛ ማለት ነው ፡ እውነተኛ ለመሆን ደግሞ ከባድ ተጋድሎን ይጠይቃል ። የተጋድሎው ዓይነትም በጽድቅ ጐዳና ካለፉት አባቶች ታሪክ መገንዘብ ይቻላል ፡ በመሠረቱ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ፡ በጽድቅ ይኖራል ። ዓለምን በጽድቅ መሥርቶአል ፡ በጽድቅም ይፈረዳል ። ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው ዋጋውን በጽድቅ ይሰጣል ፡ እንግዲህ ጻድቅ ማለት እግዚአብሔር ነው ስንል ጻድቅ የሚለው ቃልም እውነተኛ ማለት እንደሆነ እንገነዘባለን ፡ ስለዚህ መነሻውንና መድረሻውን ለማወቅ ችለናል ማለት ነው ። ነገር ግን አንድ ኃጢአተኛ ሕጉን ሳይፈጽም ሲቀር በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ ወይም በእውነት ሊቆም እንደማይችል እሙን ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ ሰው በእግዚአብሔር ፀጋ ፡ በክርስቶስ ደም ፡ በእምነት እንደሚጸድቅ በተለያዩ መልእክቶቹ ጽፎአል ፡ ነገር ግን ለአባባሉ መሠረታዊ ምክንያት እየሰጠ እንጂ በደረቅ ንባብ ያስቀመጣቸው ቃላት አለመሆኑን ያልተገነዘቡ ሰዎች "እኔ በእግዚአብሔር አምናለሁ ስለዚህ ትሩፋት ባልሠራ እንደማልኰነን አረጋግጣለሁ" ፡ ይላሉ አንዳንዶቹም ሥጋው ወደሙ ከተቀበልሁ ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው ሲሉ ይሰማሉ ፡ እንዲሁም ሐዋርያው ቅ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ" ስለሚል እኔ በጸጋው ስለጸደቅሁ በጎ ነገር መሥራት አያስፈልገኝም የሚሉም አሉ ።

እነዚህ አባባሎች የወንጌሉን ቃል በቀጥታ ይቃወማሉ "ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሁለት ዓይነት ተክሎች መሠረታዊ አቋም በምሳሌ ያስረዳል ፡ አንዱ ተክል ፍሬው ክፉ ስለሆነ ተቆርጦ ወደ እሳት እንደሚጣል ፡ ሌላው መልካም ፍሬ የሚያፈራው ደግሞ በክብካቤ እንደሚጠበቅና ጣዕም ያለውን ፍሬውንም በየጊዜው እንደሚሰጥ ይናገራል እነዚህ ሁለቱ ዛፎች የማን ምሳሌዎች ናቸው? የክፉዎቹና የደጋጎች ምእመናን ምሳሌዎች እንደሆኑ ተረጋግጦአል ። (ማቴ· ፯፡፲፯—፲፱ ።)

አንድ ዛፍ (ተክል) ልምላሜው በአንድ ሥጋዊና ምግባር አልባ ሰው ይመሰላል አንድ አጽቅ ፡ ልምላሜና መልካም ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ (ተክል) ደግሞ በአንድ እውነተኛና ትሩፋ ምግባር ምእመን ይመሰላል ። ስለሆነም በእግዚአብሰሐር ፊት በጽድቅ ደረጃ ቆመው የጽድቅ አክሊል የሚቀዳጁት በእምነታቸውና በተጋድሎአቸው ጸንተው የተቀደሰ ትሩፋት ሠርተው በመገኘታቸው ነው።

እምነት ብቻ ያድነኛል ሥጋ ወደሙ ተቀብያለሁ ይበቃኛል በጸጋው ብቻ ድኛለሁ ትሩፋት መሥራት አያስፈልገኝም ለሚሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቢታንያ ሲመለስ አንዲት የበለስ ዛፍ አየ ፡ ከእርስዋም ፍሬ ለመፈለግ ቢሄድ ከቅጠል በቀር ምንም ፍሬ ባላገኘባት ጊዜ ለዘለዓለም ፍሬ አይገኝብሽ ብሎ ረገማት እርስዋም ወዲያውኑ ከሥርዋ ደረቀች በለሲቱ የእነማን ምሳሌ ናት ? ለጊዜው የቤተ እስራኤል ምሳሌ ናት ቤተ እስራኤል በእግዚአብሐር ማመን ቀዳሚነት ሰላለን ከሁሉ እኛ እንበልጣለን ይሉ ነበር ፡ ነገር ግን እግዚአብሐር ባዘዘውና በሰጠው ሕግ ስላልተመሩ በበለሲቱ ምሳሌ ይረግማቸዋል እርግማኑ በእነርሱ ብቻ ሳይወሰን አሁንም እግዚአብሔር ያዘዘውን ጥሰው በራሳቸው ፍላጐትና በአስተሳሰባቸው የሚመሩትን ሁሉ ይመለከታቸዋል ። (ማቴ· ፳፩ ፡ ፲፯—፲፱ ።

እዚህ ላይ ከኢአማንያን ሰዎች የምንማረው ምሳሌያዊ ትምህርት አለ ። ይኸውም አንድ ገበሬ መሬቱን አርሶ ምርጥ ዘር ይዘራል ፡ ከአዝመራው ምርጥ ምርት ለማግኘት በናፍቆት ይጠብቃል እንደዚሁም መልካም ፍሬ የሚሰጡ ዛፎችን ይተክላል በወቅቱ ከዛፎቹ (ከአትክልቶቹ) መልካም ፍሬ ካላገኘባቸው እንደሚቆርጣቸው እሙን ነው ፡ ምእመናን የእግዚአብሔር አዝመራዎች ናቸው ፡ ስለሆነም እግዚአብሔር ከምእመናን የተቀደሰ ትሩፋትን ይፈልጋል ፡ ስለዚህም ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ "ወንድሞች ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል ? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን ? …" ይላል ያዕ· ፪ ፡ ፲፬—፲፯ ።

አባቶቻችን "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እንዲሉ ከሐዋርያው ቃል የምንገነዘበው እምነት ብቻ ይበቃኛል ፡ ሁሉም ነገር አያስፈልገኝም በጸጋው ድኛለሁ ፡ ሥጋ ወደሙ ከተቀበልሁ እንደምጸድቅ አረጋግጣለሁ እያሉ የሚናገሩ ዕቡዮች ፌዘኞች ተረበኞችና ዒላተኞች ይባላሉ ። ሃይማኖት (እምነት) ከምግባር ጋር ከሆነ ሰምና ፈትል ወይም ከርና ሻማ ተስማምቶ መብራት በመስጠት እንደማያገለግል ሁሉ እንደ እውነተኛ ክርስቲያንም ከእምነቱ ጋር ምግባር ሠርቶ ካልተገኘ ጻድቅ የሚያሰኝ ስም ለማግኘት እንደማይችል የታመነ ነው ።

በዚህ ቅዱስ ዓለማ የሚመሩ ሁሉ ጻድቃን ይባላሉ ጻድቃን ከዚህ ዓለም ረብና ጥቅም ስለሌላቸው በዚህ ክህደት ፡ ኑፋቄ ፤ ጥልና ክርክር በሰፈነበት ዓለም ከመኖር ይልቅ ሞትን ይመርጣሉ። ስለዚህ ነው "ሞቶሙስ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ" የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው ። የተባለው ። በሀገራችንም ሆነ በሌላው ዓለም በጽድቅ ጎዳና የሄዱ ብዙ ናቸው ፡ በዚህ አጋጣሚ በሀገራችን በጽድቅ ጎዳና ተጉዘው ወደዘለዓለም ክብር ከተሸጋገሩት መካከል ነሐሴ ፳፬ ቀን በዓለ ዕረፍታቸውን የምናከብርላቸው አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው ።

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ደብረ ጽላልሽ እቲሳ ገዳም ከፀጋ ዘአብና ከእግዚእ ሐረያ ተወለዱ በተወለዱበት ቀን ብዙ ተአምራትና ድንቅ ምልክቶች እንደታዩ መጽሐፈ ገድላቸው ይናገራል አቡነ ተክለ ሃይማኖት የቤተክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው ከተማሩ በኋላ "ዘኢየኀድግ አባሁ ወእሞ ኢይክል ይጸመደኒ" አባቱን እናቱን ያልተወ የኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም ያለውን ቃለ ወንጌል ባነበቡ ጊዜ ከናት ከባታቸው ተለይተው ወደ ሰሜን ክፍለ ሀገራት በምናኔ ሄዱ።

በቅድሚያ ለነ ሐይቅ ከነበሩት አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ጋር ተገናኝተው አምኃ መንፈሳዊ ከተለዋወጡ በኋላ ከዚያም በልዩ ልዩ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ቃለ ወንጌል ከማስተማራቸውም በላይ ታላላቅ ገዳማትንና አድባራትንም ጐብኝተዋል ። ከዚሁም በመቀጠል ወደትግራይ ሄደው በደብረ ዳሞ ገዳም ገብተው ብዙ የቅድስና ተግባር አከናውነዋል ። በመጨረሻም አርዑተ ምንኩስናውን ተቀበለው ወደላስታ በመመለስ ስለእግዚአብሐር መንግሥት በሰፊው አስተምረዋል ።

ቀጥሎም ወደሸዋ ተመልሰው "ሑሩ መወሐሩ ውስተኩሉ አጽናፈ ዓለም "እስከ ዓለም" ዳርቻ ሂዱና ፍጥረትን ሁሉ አስተምሩ ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ቃል መሠረት በብሔረ ጉራጌና በብሔረ ወላይታ በእግራቸው እየተዘዋወሩ ሕዝቡን ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እየመለሱ ጣዖታትን እያፈረሱ ሐዋርያዊ ግዳጃቸውንና የተቀደሰ ትሩፋታቸውን በቅን ፈጽመዋል" ።

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በእግዚአብሔር ምርጫ የተሾሙ ጳጳስ ስለነበሩ በአንብሮተ እድ የሾሙአቸው አበው መነኮሳትም የወንጌልን ቃል ተግተው እንዲያስተምሩ በሰጡአቸው ከባድ አደራ መሠረት በዘመናቸው የሰበኩት ወንጌል ትምህርት በመላ ኢትዮጵያ በመልካም ሁኔታ ይካሄድ እንደነበረ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ።

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን በመቀጠል በጐጃም ክፍለ ሀገርም እየተዘዋወሩ የወንጌልን ቃል በማስተማር ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል ። በመጨረሻም አጽማቸው የሚያርፍበት ቦታ ደብረ ሊባኖስ መሆኑ ስለተነገራቸው በደብረ ሊባኖስ ደብረ አስቦ በተባለው ሥፍራ የጽድቅ አክሊል ተቀዳጅተው አርፈዋል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስማቸው ልጁን የሰየመ ገድላቸውን ያጻፈ የጻፈ ፡ በስማቸው ያበላ ያጠጣ ያለበሰ ዋጋው እንደማይጠፋበት የማይታበል ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል ። የጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለ ሃየምኖት በረከትና ረድኤት በሁላችን ላይ ይሁን አሜን ።

ሊ·ት/ገብረ ክርስቶስ ኃ/ማርያም





www.ethiopianorthodox.org

# የደብረ ጽጌ ገዳም አጭር ታሪክ

ደብረ ጽጌ በኤርትራ ክፍለ ሀገር በሠራየ አውራጃ በሰፍአ ወረዳ የሚገኝ ታላቅና ቀደምትነት ካላቸው ገዳማት አንዱ ነው ፡

ገዳሙን የቆረቆሩት ጻድቁ አቡነ እንድርያስ ከአባታቸው ከበዓል ጋዳ ዘአማኑኤልና ከእናታቸው ከቅድስት ዓመተ መንፈስ ቅዱስ በትግራይ ክፍለ ሀገር በእንደርታ አውራጃ በተለይ ደርጓዓጀን በመባል ከታወቀው መንደር ተወለዱ።

ጻድቁ አቡነ እንድርያስ ከተወለዱ በኋላ በሕፃንነታቸው ይህንን ኃላፊውን ዓለም በመናቅ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከወላጆቻቸው ተለይተው በተምቤን አውራጃ ጭህ ወደ ተባለው ገዳም ገብተው በጾምና በጸሎት ተወስነው መንፈሳዊ ሥራቸውን ቀጠሉ ይህ ጭኽ የተባለውም ገዳም ያን ጊዜ ከድምፀ አራዊት በስተቀር የሰው ድምፅ የማይሰማበት በረሀ ነበር ይባላል ።

በዚህም በረሀ በልዩ ልዩ ትሩፋት ጽዋትወ መከራ ሲቀበሉ በሽተኞችን የሚፈውስ ጠበል ፈለቀላቸው ጠበሉ እስከ ዛሬ ድረስ ድውያንን ሲፈውስ በሽተኞችን ሲያድን ይኖራል ።

ጻድቁ አቡነ እንድርያስ ከጭኽ ተነሥተው ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ተሻግረው በአካለ ጉዛይ አውራጃ በሰንዓፌ ወረዳ አምባላኝ ወደሚባለው በረሀ ገብተው ሲኖሩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር ተመልሰው ዓድዋ ገቡና ከዚያው ጻድቁ አቡነ ገብረ ክርስቶስ ከሚኖሩበት ሰሎዳ በመባል ወደታወቀው ገዳም ገቡ ከዚሁ ገዳም በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ አርዑተ መንኩስና ተቀበሉ ። ከሰሎዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳምም ተነሥተው በአክሱም አካባቢ ወደሚገኘውና ደብረ ሲና ወደ ተባለው ቦታ ገብተው የተለያዩትን ተአምራት እያደረጉና አስደናቂ ሥራዎችን እየሠሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ኤርትራ



ገዳሙ የሚገኝበት ተራራ

በመሻገር በሐማሴን አውራጃ ለጎጭዋ ወደሚባለው ወረዳ በሐባላና ዴዳ እየተመላለሱ በዚሁም አካባቢ ከአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ጋር ይገናኙ ነበር ። እነዚህ ሁለት ቅዱሳን አብረው ሲኖሩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አቡነ እንድርያስንና አቡነ ኤዎስጣቴዎስን ጠርታ ሁለታችሁ መጥታችሁ በአሥመራ ባለውና በስሜ በታነጸው ቤተ ክርስቲያን እንድትቀድሱልኝ ብላ እንደነገረቻቸው የሕይወታቸውን ታሪክ የሚናገረው ገድላቸው ይመሰክራል ።

ጻድቁ አቡነ እንድርያስና ጻድቁ አቡነ ኤዎስጣቴዎስም ከሐበላ ተነሥተው ወደ አሥመራ ሲሄዱ አቡነ እንድርያስ መጻሕፍቶቻቸውን ገብርኄር በተባለው አህያቸው ጭነው ሲጓዙ በጣም ደክሞአቸው ስለነበር በፊታቸው የነበረውን ታላቅ ተራራ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ቢባርኩት ኮረብታው ተነሥቶ ከአሥመራ አልፎ ወደ ዓረበ ረቡዕ ሂዶ ቆመ ይኸውም መንገድ ሜዳ እንዲሆንላቸውና ዓቀበት እንዳይሆንባቸው ነው ።

በዚህም ጊዜ ይህንን አስደናቂውን ኃይል በማየታቸው ጻድቁ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከአቡነ እንድርያስ በዕድሜ ታናሽ ስለነበሩ አ“አቡነ ለነስ መስልክነ ሰብአ ዘክማነ ዘከመዝኑ ያፈልስ አድባረ ሃይማኖትክ “እንዲህም ማለት አባታችን ሆይ እኛስ እንደ እኛ ሰው መስለኸን ነበር እንዲህ ሁኖ ሃይማኖትህ ተራሮችን ያፈልሳልን ?

አሏቸው አቡነ እንድርያስም ልጄ ሆይ ጌታ በወንጌል የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሃይማኖት ብትኖራችሁ ተራራውን ተነሥ ብትሉት ይነሣላችኋል ያለውን አልሰማህምን ሲሉ እንደ መለሱላቸው ተጽፎ ይገኛል ።

ያ ጻድቁ አቡነ እንድርያስም ያፈረሱትም ተራረ እስከ ዛሬ ድረስ በየዓመቱ ሲቀደስበት ይኖራል ደብረ ጽዮን በመባልም ይታወቃል ።

(ወደገጽ ፲፰ ዞሯል)



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ትዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስተምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ.ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org